# የሐዋርያት ሥራ

## ትምህርት ሦስት

## ዋና ዋና መሪ ሃሳቦች

## The Book Of Acts

### Lesson Three

### Major Themes

## ተርጓሚ፡እሸቴ በለጠ

THIRD MILLENNIUM MINISTRIES

Biblical Education. For the World. For Free.

# እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓተ-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓተ-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኝ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጎሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. In 2009 ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሊ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡፡

**አስተዋፅዖ**


1. **መግቢያ**
2. **መንፈስ ቅዱስ**

ከበዓለ ሃምሳ በፊት

ጊዜ

ዓላማ

በዓለ ሃምሳ

አስፈላጊነት

ልሳን

ውጤቶች

ከበዓለ ሃምሳ በኋላ

ሰማርያ

ቂሳርያ

ኤፌሶን

3. **ሐዋርያት**

ልዩ

መመዘኛዎች

የምሥረታ ወቅት

ሥልጣን የተቀበሉ

ተግባር

በረከቶች

ተዓምራት

ራእይ

የተለያዩ

ስልቶች

መቼቶች

4. **ቤተክርስቲያን**

አስፈላጊነት

አካላዊ ውሱንነት

የዘመን ውሱንነት

ዝግጅት

ትምህርት

ቢሮዎች

መከራዎች

5. **ማጠቃለያ**

# 1. መግቢያ

ከህፃናት ልጆቻቸው ጋር ባሉ ወላጆች አካባቢ የሚገኝ ሰው ሁሉ ወላጆች ለልጆቻቸው መመሪያዎችን ደጋግመው እንደሚሰጡ ያውቃል፡፡ ልጆቻቸው የበሰሉና ፍሬያማ ሕይወትን የሚኖሩ እንዲሆኑ ለመርዳት ተመሳሳይ ሃሳቦችን ይደጋግሙላቸዋል፡፡

በተመሳሳይም መንገድ፣ እኛም የሐዋርያትን ሥራ በምናነብበት ወቅት፣ ሉቃስም አንዳንድ መሪ ሃሳቦችን ደጋግሞ ማንሳቱን ብዙም ሳንቆይ እናስተውላለን፡፡ እነዚህም የተደጋገሙ ጭብጦች የሉቃስን ትምህርት ለመረዳት ቁልፍ ሆነው በመጽሐፉ በጠቅላላ ተቀምጠዋል፡፡ ስለዚህ፣ የሐዋርያት ሥራን አስፈላጊነት ለመረዳት፣ ለእነዚህ የተደጋገሙ መሪ ሃሳቦች ጥንቃቄ የተሞላበት ትኩረት መስጠት ይገባናል፡፡

ከሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ተከታታይ ትምህርታችን ይህ ሦስተኛው ሲሆን "**ዋና ዋና መሪ ሃሳቦች**" የሚል ርዕስ ሰጥተነዋል፡፡ በዚህ ትምህርት፣ በቀደመችው ቤተክርስቲያን ዘመን ማንም ሊገታው ያልቻለውን የእግዚአብሔር መንግሥተ ወንጌል መስፋፋት ለመግለጥ ሲል ሉቃስ ደጋግሞ ያነሳቸውን ሦስት ዋና ፅንሰ-ሃሳቦች እንመለከታለን፡፡

በቀደሙት ትምህርቶች ሉቃስ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍን የጻፈበትን ዓላማ የወንጌልን መልእክት አስደናቂ ተፅዕኖ የሚተርክ ታሪካዊ ዘገባ ለማቅረብ ነው የጻፈው ብለን ጠቅልለነዋል፡፡ እንደተመለከትነው፣ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ለቀጠለው የክርስቶስ ሥራ ተዓማኒ ምስክር ይሆኑ ዘንድ ሉቃስ የታሪክን እውነታዎች ዘግቦልናል፡፡ በዚህ ትምህርት ሉቃስ ይህንን ዐቢይ ሃሳቡን ለመደገፍ የተጠቀመባቸውን ዋና ዋና መሪ ሃሳቦች በጥልቀት በመመልከት ይህንን ዓላማ የበለጠ እንመረምራለን፡፡

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ መክፈቻ ውስጥ የተገለጡትን እና በቀጣይ ምዕራፎቹ እየጎለበቱ የሄዱትን እነዚህን ሦስት ዋና ዋና መሪ ሃሳቦች እንዳስሳለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ቤተክርስቲያን የክርስቶስን መንግሥት እንድታሰፋ ኃይልን ያስታጠቃትን የመንፈስ ቅዱስን መሪ ሃሳብ እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ ስለ ክርስቶስ እንዲመሰክሩ፣ የክርስቶስንም ቤተክርስቲያን እንዲያገለግሉና እንዲመሩ በተጠሩና ሥልጣን በተቀበሉ ሐዋርያት ላይ እናተኩራለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ በየታሪክ ዘመናቱ ወንጌልና የእግዚአብሔር መንግሥት መስፋፋታቸውን እንዲቀጥሉ ለማድረግ ሐዋርያት የመሠረቷትን ቤተክርስቲያን ዋና ሃሳብ እንመለከታለን፡፡ አስቀድመን መንፈስ ቅዱስንና በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ያለውን ድርሻ እንመልከት፡፡

# 2. መንፈስ ቅዱስ

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ስለ መንፈስ ቅዱስ የዳበረ ነገረ-መለኮት ያቀርብልናል፡፡ እርሱ ቤተክርስቲያን የተለወጠ ሕይወት እንድትኖርና ዓለምን በወንጌል እንድትደርስ ለማድረግ ኃይልን የሚያስታጥቃት እንደሆነ ይነግረናል፡፡ የሐዋርያትንና የተቀሩትን የቤተክርስቲያን መሪዎች አገልግሎት ዋጋ እንዲሰጠው ለማድረግ በርካታ ምልክቶችንና ተዓምራትን እንዳደረገ ዘግቦልናል፡፡ በታላቅ መከራና ስደት ውስጥ ለሚያልፉት ክርስቲያኖች ትልቅ ብርታትን እንደሰጣቸው ይመሰክራል፡፡ በአጭሩ፣ የሐዋርያት ሥራ መንፈስ ቅዱስን የሚገልጠው የወንጌሉን እና የመንግሥቱን መስፋት በኃይል የሚያስታጥቅ ቅዱሳንም እግዚአብሔርን የሚመስል ኑሮ እንዲኖሩ የሚያስችል እንደሆነ ነው፡፡

መንፈሱ በተለያዩ መንገዶች በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ቢገለጥም፣ በሦስት ወቅቶች በቤተክርስቲያን ውስጥ የፈጠረውን ተፅዕኖ በመመልከቱ ላይ እናተኩራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ መንፈሱን ከበዓለ-ሃምሳ በፊት እንመለከተዋለን፡፡ ሁለተኛ፣ በበዓለ-ሃምሳ ዕለት በኢየሩሳሌም የመንፈሱን መፍሰስ እናያለን፡፡ ሦስተኛ

ደግሞ፣ ከበዓለ-ሃምሳ በኋላ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ እንመረምራለን፡፡ አስቀድመን የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ መንፈሱን ከበዓለ-ሃምሳ በፊት እንዴት እንደገለፀው እንመልከት፡፡

# ከበዓለ ሃምሳ በፊት

በሐሥ 1፡3-11 ውስጥ፣ በትንሣኤውና በዕርገቱ መሃል በነበረው ጊዜ ውስጥ፣ ኢየሱስ ለአርባ ቀናት ከሐዋርያቱ ጋር እንደቆየና እንዳስተማራቸው ሉቃስ ዘግቦልናል፡፡ የሐሥ 1፡3 እንዲህ ይነበባል፡

> **ደግሞ አርባ ቀን እየታያቸው ስለ እግዚአብሔርም መንግሥት ነገር እየነገራቸው፥ በብዙ ማስረጃ ከሕማማቱ በኋላ ሕያው ሆኖ ለእነርሱ ራሱን አሳያቸው። (የሐሥ 1፡3)**

እንደምንመለከተው፣ ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ካስተማራቸው ወሳኝ ነገሮች አንዱ መንፈስ ቅዱስ ወደ ሐዋርያቱ በቶሎ የሚመጣ መሆኑ ነው፡፡

ኢየሱስ ከበዓለ ሃምሳ በፊት ስለ መንፈስ ቅዱስ ያስተማራቸውን ሁለት ገፅታዎች እንዳስሳለን፡፡ በመጀመሪያ፣ የመንፈስ ቅዱስን የመምጣቱን ወቅት እንመለከታለን፡፡ ሑለተኛ ደግሞ፣ የመምጣቱን ዓላማ እንመለከታለን፡፡ አስቀድመን መንፈስ ቅዱስ ስለሚመጣበት ወቅት ኢየሱስ ያስተማረውን እንመልከት፡፡

## ወቅት

በሐሥ 1፡4-8 ኢየሱስ የተናገረውን አድምጡ፡

> **ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ። (የሐሥ 1፡8)**

ኢየሱስ የሚመጣውን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሲያውጅ፣ የእስራኤልን መንግሥት እንደገና ትመሠርታለህ ወይ የሚል ጥያቄ ሐዋርያት ጠይቀዋል፡፡ ለእስራኤል መንግሥትን ትመልሳለህን? የሚለው አገላለጥ ለዘመኑ አንባቢዎች የተለመደ አይደለም፣ ስለዚህ ቆም ብለን ማብራራት ይገባናል፡፡

የእስራኤልና የይሁዳ በደል እጅግ ከሙብዛቱ ከመሆኑ የተነሳ፣ እግዚአብሔር ከተስፋይቱ ምድር እንዲሰደዱ እንደሚያደርጋቸውና ለውጪ ገዢዎች ጭቆና አሳልፎ እንደሚሰጣቸው የብሉይ ኪዳን ነቢያት ተንብየዋል፡፡ በብሉይ ኪዳን ትንቢቶች መሠረት፣ እግዚአብሔር መሲህ እንደሚልክ፣ የህዝቡንም ኃጢአት ይቅር በማለት እንደሚያድሳቸው፣ ወደ ምድራቸውም መልሶ ገዢያቸው እንደሚሆን አይሁዶች ያምኑ ነበር፡፡ መሲሁም ከዳዊት ዘር በመሆኑ የእስራኤልና የይሁዳ ንጉሥ እንደሚሆን፣ የተስፋይቱንም ምድር የእግዚአብሔር ህዝብ ዘላለማዊና የተባረከን ሕይወት የሚኖርባት በምድር ላይ የእግዚአብሔር መንግሥት ማዕከል ያደርጋታል፡፡ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን፣ እስራኤል በሙቶዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት በእግዚአብሔር ፍርድ ስር ወድቃ ስለነበር ለእስራኤል መንግሥትን የሚመልስ ፖለቲካዊ መሲህ በጉጉት ትጠብቅ ነበር፡፡ ስለዚህ፣ ሐዋርያት ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሊያርግ መሆኑን ሲያውቁ፣ ከመሄዱ አስቀድሞ እነዚህን የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ይፈፅማል ብለው ተስፋ ያደርጉ ነበር፡፡ ለእስራኤል መንግሥትን ስለመመለሱ የጠየቁትም ለዚህ ነው፡፡ ሆኖም፣ ኢየሱስ ለእስራኤል መንግሥትን አሁኑኑ የመመለስ ህዝባዊ ናፍቆት የተሳሳተና ትንቢቶቹ የሚፈፀሙት ግን ወንጌል በምድር ሁሉ ተሰብኮ ክርስቶስ በክብር ሲመለስ እንደሆነ አስተማረ፡፡

ግን ሐዋርያት ለእስራኤል መንግሥትን የመመለሱን ጉዳይ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ስለመጠመቅ ከተናገረው ሃሳብ ጋር ለምን አያያዙት? ሐዋርያት ስለ ብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ያስቡ ስለነበር ነው፡፡ የብሉይ ኪዳን ነቢት በበርካታ ገፆቻቸው ውስጥ፣ የፍርዱ ዘመን ሲያልፍ፣ ከዚህ ቀደም ሆኖ በማያውቅ መንገድ መንፈሱን እንደሚያፈስስ ይተነብዩ ነበር፡፡

በኢሳ 44፡3-4 ነቢዩ ኢሳያስ ስለ መንፈሱ የተናገረውን አድምጡ፡

**በተጠማ ላይ ውኃን በደረቅም መሬት ላይ ፈሳሾችን አፈስሳለሁና መንፈሴን በዘርህ ላይ በረከቴንም በልጆችህ ላይ አፈስሳለሁ፥**
**በፈሳሾችም አጠገብ እንደሚበቅሉ እንደ አኻያ ዛፎች በሣር መካከል ይበቅላሉ።**
**(ኢሳ 44፡3-4)**

ኢሳያስ በዚህ ስፍራ ስለ ተሃድሶ ይናገራል፣ የሚለውም እግዚአብሔር በምድሪቱ ላይ መንፈሱን ያፈስሳል ነው፡፡

ረቢዎቹ (የህጉ መምህራን)እንደሚሉት መሲሁ ከመምጣቱ አስቀድሞ፣ እስራኤል በኃጢአት፣ በርኩሰትና በሞት ዘመን ውስጥ እንደምታልፍ የብሉይ ኪዳን ነቢት አውጀዋል፡፡ ረቢዎቹ እንደሚሉት መሲሁ ሲመጣ ደግሞ በሚመጣው ዘመን፣ የእግዚአብሔር ጠላቶች ይፈረድባቸዋል ህዝቡም በስተመጨረሻ ማንም ሊሽረው በማይቻል በረከት ይባረካል በማለትም አውጀዋል፡፡ ሂደቱ ምን ያህል ዘመን እንደሚፈጅ የብሉይ ኪዳን ነቢያት አልተናገሩም፣ አብዛኞቹ መምህራን ግን ሁሉም በአንድ ጊዜ ይሆናል ብለው ይጠብቃሉ፡፡

ከዚህ አመለካከት በተነፃፃሪ ደግሞ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት የሚገለጠው በመንግሥታት ሁሉ ዘንድ ሲስፋፋ መሆኑን ኢየሱስ አብራርቷል፡፡ ሁሉም በአንድ ጊዜ ከመምጣቱ ይልቅ፣ ወደ እግዚአብሔር የከበረ መንግሥት የሚደረገው ሽግግር ደረጃ በደረጃ የሚከናወን ይሆናል፡፡ የሚመጣው ዘመን የሚጀመረው በኢየሱስ የምድር አገልግሎት ወቅት ነው፡፡ በወንጌሉ አገልግሎት ደግሞ መንግሥቱ ሲሰፋ፣ በሰማያት በክርስቶስ ንግሥና ወቅትም ይቀጥላል፡፡ ወደፊት ኢየሱስ ተመልሶ ሲመጣ፣ ይህ የኃጢአት ዘመን ጨርሶውኑ ያበቃል፣ እናም ዓለማቀፋዊቷ፣ መሲሃዊ መንግሥት ወደ ሙላት ትመጣለች፡፡

ይህ የምትመጣዋ መንግሥት አመለካከት ኢየሱስ ለሐዋርያቱ በዚያ መንገድ ለምን እንደመለሰላቸው ያብራራልናል፡፡ መንፈስ ቅዱስ በቤተክርስቲያን ላይ ሊፈስ ያለበት ወቅት ቢሆንም፣ ይህ ማለት ግን የዘመን ሙላት ደረሰ ማለት አይደለም፡፡ ኢየሱስ ያበሰረው የመንግሥቱን መምጣት፣ ደግሞም ቤተክርስቲያን እርሱ ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ በኃጢአተኛ ዓለም ውስጥ ስትኖር ሊያስታጥቃት መንፈስ ቅዱስ እንደሚመጣ ብቻ ነው፡፡

የመንፈስ ቅዱስን የመምጣት ወቅት በልቡናችን ይዘን፣ ወደ መምጣቱ ዓላማ እንሸጋገራለን፡፡

## ዓላማ

በሐሥ 1፡8 ኢየሱስ ለሐዋርያቱ የተናገረውን አድምጡ፡

**ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ። (የሐሥ 1፡8)**

በእነዚህ ቃላት፣ ሐዋርያት ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በአዲስ መንገድ እንዲያስቡ ኢየሱስ አቅጣጫ አስይዟቸዋል፡፡ የመንግሥቱን የመጨረሻውን ሙላት ከማምጣት ይልቅ፣ ሐዋርያትን የክርስቶስ እውነተኛና ታማኝ ምስክሮች እንዲሆኑ ለማስታጠቅ መንፈስ ቅዱስ ይፈስሳል፡፡ በመንፈሱ አገልግሎት ሁለት ገፅታዎች ማለትም ኃይልና እውነተኛ ምስክርነት ላይ በማትኮር ኢየሱስ የተናገረውን ፈታ እናድርገው፡፡

በመጀመሪያ፣ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሐዋርያት ኃይልን እንደሚቀበሉ ኢየሱስ ተናግሯል፡፡ መንፈስ ከኃይል ጋር የተያያዘ መሆኑ በብሉይ ኪዳን የተለመደ ነው፣ **"የእግዚአብሔር መንፈስ"** በሚለው መግለጫ የሚወከለው ይህ ሃሳብ፣ በዕብራይስጡ *ruach elohim* (~yhiêl{a/ x:Wr) የሚለው ሃሳብ ፍቺ ነው፡፡ ይህ የዕብራይስጥ መግለጫ ስለ ብርቱ ንፋስ ወይም ከእግዚአብሔር ስለሚሰጥ ኃይል የሚናገር ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን፣ የእገዚአብሔርን ፈቃድ በምድር ለማምጣት መንፈስ ቅዱስ በኃይል ይሠራ ነበር፡፡

በተጨማሪም መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ሕይወት ውስጥ አስደናቂ በሆነ መንገድ በኃይል ይገለጥ ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ በመሳፍንት ምዕራፍ 14-15፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በሶምሶን ላይ በኃይል ሲመጣ፣ እስራኤል በጠላቶቿ በፍልስጥኤማውያን ላይ ድልን የምትቀዳጅባቸውን ተዓምራዊ ጀብዱዎች ይፈፅም ነበር፡፡

ከመንፈሱ ኃይል በተጨማሪ፣ መንፈሱ ደቀመዛሙርቱ እውነተኛ ምስክሮች እንዲሆኑ ያደርጋቸው እንደነበር ኢየሱስ ጠቅሷል፡፡ ይህም ተዛምዶ በብሉይ ኪዳንም ተንፀባርቋል፡፡ በበርካታ ጊዜያት፣ ህዝቡ ስለ እግዚአብሔር በድፍረትና በውጤታማነት እንዲናገር የእግዚአብሔር መንፈስ ኃይልን ሰጥቷል፡፡ ለምሳሌ፣ በሚክያስ 3፡8 የተጠቀሰውን አድምጡ፡

> ***እኔ ግን … በእግዚአብሔር መንፈስ ኃይልንና ፍርድን ብርታትንም ተሞልቻለሁ። (ሚክያስ 3፡8)***

በዚህ ምንባብ፣ ሚክያስ ምንም እንኳን ሃሰተኛ ነቢያት ቢቃወሙትም መንፈሱ እውነቱን እንዲናገር ደፋር አድርጎት ነበር፡፡

ስለዚህ፣ ሐዋርያት የእርሱ ምስክር እንዲሆኑ ለማስታጠቅ በመንፈስ ቅዱስ እንደሚጠምቃቸው ኢየሱስ ሲነግራቸው፣ መንፈሱ በሌሎች ላይ በብሉይ ኪዳን ሲያደርግ እንደነበረው በእነርሱም ውስጥ እንደሚሠራ እያመለከተ ነው፡፡ በተጨማሪም መንፈስ ቅዱስ የሐዋርያትን መልእክት እውነተኝነት ለማረጋገጥ እና ለሚቃወሟቸውም የሚሰጡትን መልስ ሊያቀብላቸው የኃይልን ተግባራት ይፈፅም ነበር፡፡ በእርግጥም እነዚህ የመንፈሱ መገለጫዎች በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ደጋግመው ይገለጡ ነበር፡፡

ከበዓለ ሃምሳ በፊት ሉቃስ መንፈስ ቅዱስን ያስተዋወቀበትን ጥቂት መንገዶች ከተመለከትን፣ በኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን በተሰበሰበችበት በበዓለ ሃምሳ ወደ ፈሰሰው መንፈሱ እንሸጋገር፡፡

## በዓለ ሃምሳ

የሐሥ 2፡1-4 መንፈስ ቅዱስ በቤተክርስቲያን ላይ የመፍሰሱን ዘገባ ይዟል፡፡

> ***በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፥ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ፥***
> ***ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፥ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው።***

***እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው፤ በያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው።***
***በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር። (የሐሥ 2፡1-4)***

የዚህን ወቅት ወሳኝነት ለመመርመር፣ ሦስት ጉዳዮችን እንዳስሳለን:: በመጀመሪ፣ የበዓለ ሃምሳን ወሳኝነት እንመለከታለን:: ሁለተኛ፣ በልሳን የመናገርን ክስተት እንዳስሳለን:: ሦስተኛ ደግሞ፣ የዚህን ወቅት ውጤቶች እንወያይበታለን:: አስቀድመን የበዓለ ሃምሳን አስፈላጊነት እንመልከት::

## አስፈላጊነት

በዓለ ሃምሳ በእስራኤል ቅዱስ የዘመን መቁጠሪያ ከፋሲካ ጋር የቅርብ ቁርኝት ያለው የበዓል ወቅት ነው:: ዘፀአት 12 እና ዘሌዋውያን 23 እንደሚነግሩን፣ ፋሲካ እስራኤላውያን ከግብፅ ነፃ የወጡበትን ጊዜ የሚያስታውሱበት ወቅት ነው:: እግዚአብሔር የግብፅን በኩር ሁሉ ሲገድል ታማኝ የነበሩ እስራኤላውያንን ቤት ያለፈበትን፣ የመቅሰፍቱን የመጨረሻ ሌሊት ያስባሉ:: የፋሲካ በዓል እግዚአብሔር አይድን ከግብፅ ባርነት ነፃ ያወጣበትን መንገድ ያስታውሳቸዋል::

በዓለ ሃምሳ የሚከበረው በመጀመሪያው የመከር ወቅት ከፋሲካ ሃምሳ ቀናት ካለፈ በኋላ ነበር:: ከመጀመሪያው ይከበር የነበረው በተስፋይቱ ምድር እንዲፀኑ የእግዚአብሔርን መግቦት ለማሰብ ነው:: በዚህ ወቅት ደግሞ፣ እስራኤላውያን በዚያን ዓመት እናገኘዋለን ብለው ተስፋ ከሚያደርጉት መከር የመጀመሪያውን ፍሬ እንደ ምስጋና መስዋዕት የሚያቀርቡበት ነበር::

ከዚህም በተጨማሪ፣ በአዲስ ኪዳን ዘመንም አይሁድ በዓለ ሃምሳን ሲያከብሩ እግዚአብሔር ለሙሴ ህጉን የሰጠበትን ጊዜም ያስባሉ:: መንፈስ ቅዱስ በዚህ ወቅት መፍሰሱ ለቀደመችውም ቤተክርስቲያን አስፈላጊ ነበር ምክንያቱም በነቢዩ በኤርምያስ የተነገረውን ተስፋ ስለሚያሳስባቸው ነው::

ነቢዩ በኤርምያስ 31፡31-33 ምን እንደጻፈ አድምጡ፡

***እነሆ፥ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል፥ ይላል እግዚአብሔር***
***ከግብጽ አገር አወጣቸው ዘንድ እጃቸውን በያዝሁበት ቀን ከአባቶቻቸው ጋር እንደ ገባሁት ያለ ቃል ኪዳን አይደለም እነርሱ በኪዳኔ አልጸኑምና፥ እኔም ቸል አልኋቸው፥ ይላል እግዚአብሔር፡-***
***ከእነዚያ ወራት በኋላ ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ቃል ኪዳን ይህ ነውና፥ ይላል እግዚአብሔር ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፥ በልባቸውም እጽፈዋለሁ እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል። (ኤር 31፡31-33)***

በልብ ውስጥ የህጉ መጻፍ በብሉይ ተስፋ የተሰጠበትና በአዲስ ኪዳን የተፈጸመው የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራ ነው::

ይህንን የብሉይ ኪዳንን ዳራ ለመጠበቅ፣ በሐሥ 2 እንደተጠቀሰው በበዓለሃምሳ ዕለት የመንፈሱ መፍሰስ ለክርስቲያን ቤተክርስቲያን አስፈላጊ ነው:: ኢየሱስ በመስቀል የሞተው በፋሲካ ክብረ በዓል ዕለት ነው::

የእግዚአብሔርን ህዝብ ከኃጢአትና ከሞት ባርነት ነፃ ያወጣ ዘንድ፣ የመጨረሻው የፋሲካ ጠቦት ሆኖ ሞተ፡፡

ጳውሎስ በ፤ቆሮ 5፡7 እንዲህ አስቀምጦታል፡

***ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶአልና፤ (፤ኛ ቆሮ 5፡7)***

በዚህ መሠረት፣ በበዓለ ሃምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ መፍሰሱ አስገራሚ አይሆንም፡፡ በዓለ ሃምሳ ወደ ታላቁ መከር ትኩረትን እንደሚስብ ሁሉ፣ የመንፈሱም መምጣት የሚመጣው ዘላለማዊ ድነት የበኩራት ፍሬ ነው፡፡ በመጀመሪያው የክርስቲያኖች በዓለ ሃምሳ ዕለት የመንፈሱ መምጣት ቤተክርስቲያን በሰዎች ልብ የተጻፈውን የእግዚአብሔር ህግ መቀበሏን እና ደፋር ምስክር አድርጎ የሚያስታጥቃት መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ጳውሎስ በሮሜ 8፡23 እንዳመለከተው፣ ክርስቲያኖች፡

***…የመንፈስ በኩራት ያለን … (ሮሜ 8፡23)***

ሉቃስ ስለ መንፈሱ መፍሰስ የራሱን ዘገባ ሲያሰፍር፣ ስለ ተከናወነው ነገር አስፈላጊነት ለማመልከት ሲል ከበዓለ ሃምሳ ጋር ባለው ትስስር ላይ አጽንዖት ሰጥቷል፡፡ ተራ ክስተት አልነበረም፤ ከብዙ ተዓምራት መካከል አንዱ ብቻም አልነበረም፡፡ በበዓለ ሃምሳ ቀን የመንፈሱ መሰጠት ታላቁ የድነት መከር የተጀመረበት እና መሲሐዊውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመመሥረት የእግዚአብሔር ህዝብ ውስጣዊ ተሃድሶ የተገኘበት ነው፡፡

የበዓለ ሃምሳን አስፈላጊነት የመንፈሱ መፍሰስ ወቅት ከመሆኑ ጋር የተሳሰረ እንደሆነ ከተረዳን፣ አሁን ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ መገኘት መገለጫ ሆኖ ስለተገለጠው በልሳን የመናገር ክስተት እንሺጋገር፡፡

## ልሳኖች

በሐዋርያት ሥራ 2 ውስጥ፣ በበዓለ ሃምሳ ቀን የእግዚአብሔር መንፈስ በቤተክርስቲያን ላይ ስለ መፍሰሱ ሉቃስ ሲዘግብ፣ ሐዋርያትና ሌሎች አማኞች በሌሎች ልሳኖች ተናገሩ፡፡ እንደ አለመታደል ሆኖ ግን በልሳን የመናገርን ስጦታ አስመልክቶ በቤተክርስቲያን ውስጥ ብዙ ግራ መጋባት አለ፡፡ ስለዚህ፣ በሁለት ጥያቄዎች ላይ ሃሳብ ለመሰንዘር ጊዜ እንውሰድ፡፡ በመጀመሪያ፣ የልሳን ስጦታ ምን ነበር? ሁለተኛ ደግሞ፣ እግዚአብሔር ይህን ስጦታ ለምን ሰጠ?

በዘመናችን ቤተክርስቲያን፣ የተለያዩ ክርስቲያኖች የልሳንን ስጦታ በተለያዩ መንገዶች ይረዳሉ፡፡ አንዳንዶቹ ልሳኖች ከመናገር ይልቅ የመስማት ተዓምር በማለት ይከራከራሉ፡፡ በዚህ አመለካከት፣ አድማጮቹ በየራሳቸው ቋንቋ ይረዱ ዘንድ ሐዋርያት እጅግ አስደሳች ንግግር ተናግረዋል፡፡

ሆኖም ከሉቃስ አገላለጥ ቢያንስ ሁለቱ ገፅታዎች ተዓምሩ በአንድ ወገን መናገርን የያዘ ሲሆን፣ በአንዱ ደግሞ የቀደሙት ክርስቲያኖች ከዚያ በፊት በማያውቋቸው ሰብዓዊ ቋንቋዎች መናገራቸውን ያመለክታል፡፡ የመጀመሪያውና ከሁሉ የሚልቀው፣ ተናጋሪዎቹ በሌላ ቋንቋ መናገር ይችሉ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ያስቻላቸው መሆኑን ሉቃስ በግልፅ ጽፏል፡፡ በሐሥ 2፡4 እንዲህ ይነበባል፡

***በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።*** *(ሐሥ 2፡4)*

አድማጮቹ በተዓምር ማድመጥ ይችሉ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ሞላቸው የሚል ምንም ፍንጭ ሉቃስ አልሰጠንም:: ሁለተኛ፣ “ልሳን” የሚለው ቃል glōssa የተሰኘው የግሪክ ስም ትርጓሜ ነው:: በአዲስ ኪዳንና በሌሎችም የግሪክ ስነ-ጽሑፎች፣ ይህ ቃል መደበኛውን ሰብዓዊ ቋንቋ የሚያመለክት ነው:: በዚህ አውድ መሠረት ሌላ ፍቺ አለው ብለን ልንጠረጥር የምንችልበት ምንም የተጨበጠ ምክንያት የለም:: ስለዚህ፣ በበዓለ ሃምሳ ቀን የተሠጠው የልሳን ተዓምራዊ ስጦታ ሰዎች የማያውቁትን ሰብዓዊ ቋንቋ መናገር የሚችሉበት ብቃት ነው::

ግን መንፈስ ቅዱስ መገኘቱን በዚህ ልዩ መንገድ ለምን አደረገው? በዚያ ቀን የልሳን አስፈላጊነቱ ምንድን ነው? በሐሥ 2፡16-21 ጴጥሮስ የሰጠውን መግለጫ አድምጡ፡

***ነገር ግን ይህ በነቢዩ በኢዩኤል የተባለው ነው።***
***እግዚአብሔር ይላል። በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፤ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፥ ጎበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ፥ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልም ያልማሉ፤***
***ደግሞም በዚያች ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎቼ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ ትንቢትም ይናገራሉ።***
***ድንቆችን በላይ በሰማይ፥ ምልክቶችንም በታች በምድር እሰጣለሁ፤ ደምም እሳትም የጢስ ጭጋግም ይሆናል፤***
***ታላቅ የሆነ የተሰማም የጌታ ቀን ሳይመጣ ፀሐይ ወደ ጨለማ ጨረቃም ወደ ደም ይለወጣሉ።***
***የጌታን ስም የሚጠራም ሁሉ ይድናል። (ሐሥ 2፡16-21)***

በዚህ ምንባብ፣ በበዓለ ሃምሳ ቀን፣ የልሳን ተዓምራዊ ስጦታን ጨምሮ ምን እንደተከናወነ ለማብራራት ጴጥሮስ ኢዩኤል 2፡28-32 አጣቅሷል::

በሚያስገርም መንገድ፣ ጴጥሮስ የኢዩኤን ቃል በቀጥታ አልጠቀሰውም:: በዕብራውያን መጽሐፍ ቅዱስና በሰብዓ-ሊቃናት፣ የኢዩኤሉ ምንባብ የሚጀምረው “ከዚህም በኋላ እንዲህ ይሆናል መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ” በማለት ነው:: ጴጥሮስ ግን ኢዩኤል 2፡28 በማሳጠር “በመጨረሻው ቀን” ይላል:: ጴጥሮስ የኢዩኤልን ቃል መለወጡ የሚያመለክተው በበዓለ ሃምሳ ቀን የተከናወኑት ነገሮች የመጨረሻው ቀን አካል መሆኑን ነው::

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የፈሰሰው በመጨረሻ ው ቀን የመሆኑ የጴጥሮስ እምነት ከኢዩኤል በጠቀሳቸው ሌሎች ቃላትም የተደገፈ ነበር:: ጴጥሮስ በኢዩኤል 2 እንደጠቀሰው መንፈሱ የሚመጣው ታላቁና የከበረው የጌታ ቀን ሳይመጣ በፊት መሆኑን አመልክቷል::

በጠቅላላው ብሉይ ኪዳን፣ የጌታ ቀን የእግዚአብሔር የፍርድና የበረከት ቀን ነበር:: በብሉይ ኪዳን በበርካታ ወቅቶችም፣ በስተመጨረሻው እግዚአብሔር ጠላቶቹን ሁሉ ድል የሚነሳበትን እና የታመነ ህዝቡን የሚባርክበትን ቀን የሚያመለክት ነው::

ስለዚህ፣ ጴጥሮስ የመንፈሱን መፍሰስ የጌታ ታላቅና ክቡር ቀን መገለጫ አድርጎ ሲያብራራ፣ በበዓለ ሃምሳ ቀን የሆነው ነገር በታሪክ ውስጥ ታላቅ ክስተት መሆኑን እየተናገረ ነው:: በበዓለ ሃምሳ መንፈሱ የመጣው

የመጨረሻው ቀን፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት የመጨረሻ እርከን የሚመሠርት የከበረ መለኮታዊ የጉብኝት አስደናቂ እለት መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡

የሚያሳዝነው ግን፣ በዚህ ዘመን በርካታ ክርስቲያኖች የመንፈሱን መፍሰስ ዐቢይ ወሳኝነት ይስቱታል፡፡ ይልቁኑ፣ በሐስ 2 የተከናወኑትን ነገሮች ለክርስቲያኖች ግላዊ ቅድስና ሞዴል አድርገው ማሰባቸው የተለመደ ሆኗል፡፡ እውነተኛ መንፈሳዊ የሆኑ ክርስቲኖች በበዓለ ሃምሳ እለትና በሌሎችም በሐዋርያት ሥራ በተጠቀሱ ወቅቶች እንደሆነው የመንፈስ ቅዱስን ድራማዊ መገለጫ ሊለማመዱ ይገባል የሚል የራሳችንን ምኞት ፈጥረናል፡፡

እስኪ እንዲህ ብላችሁ አስቡ፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችን መምጣቷን ለማወጅ በርካታ የእግዚአብሔር ታላላቅና አስደናቂ ሥራዎች እንደሚከናወኑ አዲስ ኪዳን ያስተምረናል፡፡ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፣ ከሞትም ተነሣ ደግሞም በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተቀመጠ፡፡ ሰው በክርስቶስ ወደ ማመን ሲመጣ፣ በዚያ ሰው ሕይወት ውስጥ የእነዚህ ክስተቶች ትሩፋቶች ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡ ግን ሰው በክርስቶስ ባመነ ቁጥር ክርስቶስ አይሞትም፣ አይነሣም ደግሞም አያርግም፡፡

በተመሳሳይም መንገድ፣ በዓለ ሃምሳ እግዚአብሔር የመጨረሻውን ቀን የገለጠበት ጣላቅና የአንድ ወቅት ክስተት መሆኑን መንፈስ ቅዱስ ያስተምረናል፡፡ በዚህ ትምህርት ወደ ኋላ ላይ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በሌሎችም ወቅቶች መንፈስ ቅዱስ በልዩ ሁኔታ ሲፈስስ ተመሳሳዩ ነገር እንደተከሰተ እንመለከታለን፡፡ ከመጀመሪዎቹ የክርስቲያን ቤተክርስቲያናት አንስቶ እስካሁን ድረስ፣ የመንፈስ ቅዱስ መገኘት እና ለአገልግሎት እኛን ማስታጠቁ እንደቀጠለ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ በሚያምኑት ሕይወት ውስጥ ሊኖር እንደሚገባ እንጠብቃለን፣ ሆኖም ልክ በበዓለ ሃምሳ እንደሆነው ዓይነት መገለጫ ዛሬም እንዲሆን መጠበቅ የለብንም፡፡ እንዲያውም፣ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ በልዩ መንገድ በፈሰሰባቸውም ስፍራዎች የነበረው መገለጫ ከበዓለ ሃምሳው ጋር በቀጥታ አንድ አይነት አልነበረም፡፡ በበዓለ ሃምሳ የታዩት እንደ እሳት የተከፋፈሉ የሚታዩ ልሳኖች፣ እንደሚነጥቅ የአውሎነፋስ ድምፅ ከሰማይ፣ ደግሞም የትንቢትና የልሳን ስጦታዎች፣ በቀጥታ መደበኛ ክርስቲያን ልምምዶች አልነበሩም፡፡ እግዚአብሔር የመንግሥቱን ብሥራት ያወጀባቸው፣ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ጣልቃ ገብነት ሥራዎች መገለጫ ነበሩ፡፡

የበዓለ ሃምሳን አስፈላጊነት እና የመንፈስ ቅዱሱን መፍሰስ ተከትሎ የመጣውን የልሳን ተዓምራዊ ስጦታ ከተመለከትን፣ በዚያ ቀን የተከናወኑት ነገሮች ወዳስከተሉት ውጤት እንሸጋገር፡፡

## ውጤቶች

እንደምታስታውሱት፣ ቀደም ብለን በዚህ ትምህርት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የተሰጠው ሐዋርያት የእርሱ ደፋር አምላካዊ ምስክሮች ይሆኑ ዘንድ ኃይልን ሊያለብሳቸው መሆኑን ኢየሱስ ተናግሯል፡፡ ስለዚህ፣ የበዓለ ሃምሳን ውጤቶች ስንነጋገርባቸው፣ መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት ኃይልን የሰጠበትን መንገድና ይህንንም ኃይሉን የመንግሥቱን ወንጌል የማስፋቱን ሥራ ለመባረክ እንደተጠቀመበት በመመልከቱ ላይ እናተኩራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ መንፈስ ቅዱስ ሐዋርያው ጴጥሮስን ኃይል ያለበሰበትን መንገድ እናያለን፡፡

የሉቃስን ወንጌል ስንዳስስ፣ መንፈስ ቅዱስ ከመምጣቱ አስቀድሞ፣ ጴጥሮስ ዘወትር ሃሳቡ ግልፅ ያላለለት ሰው ነበር፡፡ ለሙሴና ለኤልያስ ድንኳን ለመትከል በመፈለጉ ምክንያት በመገለጥ ተራራ ላይ ተነቅፏል፡፡ ጌታ በተያዘባት ሌሊት ክርስቶስን ሦስት ጊዜ ክዶታል፡፡ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ጴጥሮስ በሰጠው አገልግሎት ውስጥም እንኳን፣ ጴጥሮስ ከፍተኛ ትምህርት ያልተማረና ማራኪ በሆነ መንገድ እንዲናገር የሚጠበቅ ዓይነት ሰው እንዳልሆነ ሉቃስ እንድናስተውል ያደርገናል፡፡ በሐሥ 4፡13 ሉቃስ የተናገረውን አድምጡ፣

***ጴጥሮስና ዮሐንስም በግልጥ እንደ ተናገሩ ባዩ ጊዜ፥ መጽሐፍን የማያውቁና ያልተማሩ ሰዎች እንደ ሆኑ አስተውለው አደነቁ፥ ከኢየሱስም ጋር እንደ ነበሩ አወቁአቸው፤ (ሐሥ 4፡12)***

ይህንን የጴጥሮስን ምስል ስናስተውል፣ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደለወጠው እና ያንን የመሰለ ድንቅና ውጤታማ የወንጌል መልእክት በበዓለ ሃምሳ ቀን እንዲያስተላልፍ እንደረዳው አያጠራጥርም፡፡ በበዓለ ሃምሳ ስብከቱ፣ ክርስቲያኖች ሰክረዋል ብለው የተናገሩትን ጴጥሮስ አስተባብሏል፡፡ ኢየሱስ እርሱ በትንቢት የተነገረው መሲህ መሆኑን በመግለጥ፣ ከብሉይ ኪዳን ጠቅሷል፣ ተርጉሟል ደግሞም አሳማኝ በሆነ መንገድ አዛምዷል፡፡ የእነርሱ አዋጅ እውነት የመሆኑ ምስክር እንዲሆንም መንፈስ ቅዱስ ጴጥሮስና ሌሎቹ ሐዋርያት ተዓምራትን እንዲያደርጉ አስችሏቸዋል፡፡ በሐሥ 2፡43 እንዲህ እናነባለን፡

***ነገር ግን በሰው ሁሉ ፍርሀት ሆነ፤ በሐዋርያትም እጅ ብዙ ድንቅና ምልክት ተደረገ። (ሐሥ 2፡43)***

ጴጥሮስና ሌሎቹ ሐዋርያት የወንጌሉ አዋጅ ምስክሮች ይሆኑ ዘንድ፣ መንፈስ ቅዱስ የሰጠውን ይህንን ታላቅ ኃይል ስንመለከት፣ እግዚአብሔር የሐዋርያትን ምስክርነት መባረኩ አያስገርመንም፡፡ በሐሥ 2፡41፣47 ምስክርነታቸውን ሉቃስ እንዴት እንደገለጠው አድምጡ፡

***ቃሉንም የተቀበሉ ተጠመቁ፥ በዚያም ቀን ሦስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመሩ፤… ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር። (ሐሥ 2፡41፣47)***

በበዓለ ሃምሳ ቀን ሦስት ሺህ ሰዎች አመኑ! ይህ ውጫዊ፣ የቁጥር እድገት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካይነት የመጣ ነበር፡፡ የቤተክርስቲያን እድገት ግን ውጫዊ ብቻ አልነበረም፡፡ ከመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተነሳ ውስጣዊ እድገትም ይታይ ነበር፡፡ ሐሥ 2፡42-47 የተቀመጠውን አድምጡ፡

***በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር።
ነገር ግን በሰው ሁሉ ፍርሀት ሆነ፤ በሐዋርያትም እጅ ብዙ ድንቅና ምልክት ተደረገ።
ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ፤
ያላቸውንም ሁሉ አንድነት አደረጉ። መሬታቸውንና ጥሪታቸውንም እየሸጡ፥ ማንኛውም እንደሚፈልግ ለሁሉ ያካፍሉት ነበር።
በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ፥ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፤
እግዚአብሔርንም ያመሰግኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር። (ሐሥ 2፡42-47***

ክርስቲያኖች በሐዋርያት አስተምህሮ መሠረት ሲኖሩ፣ መሰል አማኞችንና እግዚአብሔርን ለማገልገል ራሳቸውን ሲሰጡ ቤተክርስቲያን በውስጣዊ ረገድ ታድጋለች፡፡ በበዓለ ሃምሳ ቀን የመንፈሱ መፍሰስ በቤተክርስቲያን የመጀመሪያ ዓመታት ውስጥ ያስገኛቸው ውጤቶች አስገራሚዎች ነበሩ፡፡

ከበዓለ ሃምሳ በፊት እና በበዓለ ሃምሳ ቀን ስለ መንፈስ ቅዱስ ሉቃስ ያቀረበውን ዘገባ ከተመለከትን፣ የወንጌሉን አገልግሎት በኃይል ለማስታጠቅ ከበዓለ ሃምሳ በኋላ በቀጣይነት መንፈስ ቅዱስ የሠራበትን መንገድ እንመለከታለን፡፡

## ከበዓለ ሃምሳ በኋላ

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ፣ ከበዓለ ሃምሳ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ስለ ሠራቸው አስደናቂ ሥራዎች ሉቃስ መላልሶ ያነሳል፡፡ ለማብራራት ያህል ከእነዚህ ምንባቦች መሃል በሦስቱ ላይ እናተኩራለን፡፡ በመጀመሪያ በሰማርያ ስሟ ባልተጠቀሰው በአንድ ከተማ የሆነውን እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ በቂሳርያ የተከሰተውን እናያለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ በኤፌሶን የመንፈሱን መገለጥ እንዳስሳለን፡፡ በመጀመሪያ በኢየሩሳሌም በስተሰሜን በሰማርያ የተከሰተውን የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት እንይ፡፡

### ሰማርያ

በሐሥ 8፡14-17፣ መንፈስ ቅዱስ ለየት ባለ መንገድ በአማኞች ላይ የመጣበትን ሌላ ወቅት ሉቃስ ይዘግባል፡፡ ሉቃስ በዚያ ስፍራ ምን እንደጻፈ አድምጡ፡

> ***በኢየሩሳሌምም የነበሩት ሐዋርያት የሰማርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንደተቀበሉ ሰምተው ጴጥሮስንና ዮሐንስን ሰደዱላቸው።***
> ***እነርሱም በወረዱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ ጸለዩላቸው፤***
> ***በጌታ በኢየሱስ ስም ብቻ ተጠምቀው ነበር እንጂ ከእነርሱ በአንዱ ላይ ስንኳ ገና አልወረደም ነበርና።***
> ***በዚያን ጊዜ እጃቸውን ጫኑባቸው መንፈስ ቅዱስንም ተቀበሉ። (ሐሥ 8፡14-17)***

በጥቅሉ በሐዋርያት ሥራ (ልክ እንደዛሬው)፣ ሰዎች በመጀመሪያ ወደ እምነት ሲመጡ መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ላይ ይፈስስ ነበር እንጂ ካመኑ በኋላ ቆይቶ አልነበረም፡፡ በዚህ ረገድ፣ በዚህ ስፍራ የሆነው ከበዓለ ሃምሳ ጋር ይመሳሰላል፡፡ አማኞች መንፈስ ቅዱስን ካመኑ በኋላ ይቀበላሉ፡፡ ይህ ወቅት መንፈሱ ድራማዊ በሆነ መንገድ የፈሰሰበት ልዩ ወቅት ነው፡፡ መንፈሱ ወደ ሳምራውያን በዚህ መንገድ ለምን መጣ?

መንፈሱ ባልተለመደ መንገድ መፍሰሱን የምናብራራበት የተሻለው መንገድ፣ ሳምራውያን በብዙ ቁጥር በማመን ወደ ክርስትና የመጡ መሆናቸውን ለማመልከት ነው የሚለው ነው፡፡ እንደምታስታውሱት፣ ሐዋርያት የእግዚአብሔርን መንግሥት በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳ፣ በሰማርያና በምድር ዳርቻ ሁሉ እንዲያሰፉ ኢየሱስ ልኳቸው ነበር፡፡ በይሁዳ በምትገኘው ኢየሩሳሌም በበዓለ ሃምሳ ቀን ጅማሬው ሆነ፡፡ ሳምራውያን ግን ቅይጥ ዘር ነበሩ፣ ማለትም አይሁድና አህዛብ፣ እናም እግዚአብሔርን ብሉይ ኪዳን እንደሚያስተምረው አያመልኩም ነበር፡፡ ስለዚህ፣ ወንጌል ወደ ሰማርያ ሲደርስ፣ ማለትም ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የሰጠው ተልዕኮ ስኬት ወደ አዲስ ዐቢይ እርከን መሻገሩን ይወክላል፡፡ ወንጌል የትውልድን ድንበር የተሻገረበት የመጀመሪያ ዋና መስፋፋት ነበር፡፡ መንፈስ ቅዱስ እነዚህን አማኞች በልሳን እንዲናገሩ ያደረጋቸው ሳምራውያን በሙላት በቤተክርስቲያን ውስጥ እንዲዋሃዱ ለሐዋርያትና ለጠቅላላው ቤተክርስቲያን ምስክርነት ለመስጠት ነበር፡፡

መንፈስ ቅዱስ በሰማርያ የሰጠውን ይህንን አገልግሎት በልቡናችን ይዘን፣ ወደ ቂሳርያ፣ ማለትም መንፈስ ቅዱስ አንድ ጊዜ በበዓለ ሃምሳ የሆነውን ለማሳሰብ በቤተክርስቲያን ላይ መምጣቱን ወደመመልከት እንሸጋገራለን፡፡

### ቂሳርያ

ስሟ ባልተጠቀሰው የሰማርያ ከተማ እንደሆነው ሁሉ፣ ወንጌል ወደ አዲስ የትውልድ ድንበር ለመጀመሪያ ጊዜ መሻገሩን ሁኔታው ያመለክተናል፡፡ በዚህ ረገድ፣ አህዛብ በብዙ ቁጥር ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ክርስቶስ ይመጣሉ፣ በተለይም የሮማዊው መቶ አለቃ ቆርኔሌዎስና ቤተሰቡ ተጠቅሰዋል፡፡

የሐሥ 10፡44-47 ጴጥሮስ ለቆርኔሌዎስ ቤተሰብ ወንጌልን ሲሰብክ ምን እንደሆነ ዘግቧል፡

> ***ጴጥሮስ ይህን ነገር ገና ሲናገር ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደ።***
> ***ከጴጥሮስም ጋር የመጡት ሁሉ ከተገረዙት ወገን የሆኑ ምዕመናን በአሕዛብ ላይ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ስለ ፈሰሰ ተገረሙ፤***
> ***በልሳኖች ሲናገሩ እግዚአብሔርንም ሲያከብሩ ሰምተዋቸዋልና።***
> ***በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ መልሶ፦ እነዚህ እንደ እኛ ደግሞ መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉ እንዳይጠመቁ ውኃን ይከለክላቸው ዘንድ የሚችል ማን ነው? አለ።***
> ***(የሐሥ 10፡44-47)***

አንድ ጊዜ በድጋሚ፣ ከበዓለ ሃምሳ ጋር የሚሄድ አስገራሚ ተጓዳኝ ክስተት ይገለጣል፡፡ በወንጌል ያመኑት በልሳን መናገር ጀምረዋል፡፡ ጴጥሮስም የቂሳርያ ሰዎች ልክ እንደኛ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ ሲል ተናግሯል፡፡ ምናልባትም የሚያጣቅሰው በበዓለ ሃምሳ የመንፈሱን መፍሰስ ሊሆን ይችላል፡፡

በብሉይ ኪዳን፣ አህዛብ እግዚአብሔር ለእስራኤል ከሰጠው ልዩ ኪዳን ውጪ ነበሩ፡፡ ታማኝ የሆኑት አይሁድ ራሳቸውን ካልተለወጡ አህዛብ ዘወትር ያርቁ ነበር፡፡ ስለዚህ፣ አህዛብ አስቀድመው ሙሉ በሙሉ ወደ ይሁዲነት ሳይገቡ ወደ ክርስትና መምጣታቸው ለቀደመችው ቤተክርስቲያን አስገራሚ ነበር፡፡

በማስከተልም፣ መንፈስ ቅዱስ በቆርኔሌዎስና በቤቱ ሁሉ ላይ በዚህ አስደናቂ መንገድ ፈሰሰ ይህም በስተመጨረሻ በሩ ለአህዛብም መከፈቱን ገለጠ፡፡ ቤተክርስቲያን ስለ አህዛብ መለወጥ የሰጠችውን ምላሽ ሉቃስ በሐሥ 11፡4፣15 እና 18 ያሰፈረውን አድምጡ፡

> ***ጴጥሮስ ግን ከመጀመሪያው ጀምሮ በተራ ገለጠላቸው እንዲህም አለ፦ … ለመናገርም በጀመርሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ለእኛ ደግሞ በመጀመሪያ እንደ ወረደ ለእነርሱ ወረደላቸው። … ይህን በሰሙ ጊዜም ዝም አሉና። እንኪያስ እግዚአብሔር ለአሕዛብ ደግሞ ለሕይወት የሚሆን ንስሐን ሰጣቸው እያሉ እግዚአብሔርን አከበሩ። (የሐሥ 11፡4፣15፣18)***

ከበዓለ ሃምሳው ጋር በሚስማማ መንገድ በአህዛብ ላይ በመምጣት፣ ለውጣቸው እውነተኛ መሆኑን፣ መንግሥቱንም በአህዛብ አማካይነት የማስፋት እቅዱ መጀመሩን መንፈስ ቅዱስ ገለጠ፡፡

በሰማርያና በቂሳርያ መንፈሱ የሠራውን ከተመከትን፣ አሁን ደግሞ በኤፌሶን ምን እንደተከናወነ እንመለከታለን፡፡

**ኤፌሶን**

ይህ ሁኔታ የተዘገበው፣ የሚከተለውን በምናነብበት በሐሥ 19፡1-6 ውስጥ ነው፡፡

> ***አጵሎስም በቆሮንቶስ ሳለ ጳውሎስ በላይኛው አገር አልፎ ወደ ኤፌሶን መጣ፥ አንዳንድ ደቀ መዛሙርትንም አገኘ። ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን፧ አላቸው። እርሱም፦ አልተቀበልንም መንፈስ ቅዱስ እንዳለ ስንኳ አልሰማንም አሉት።***
> ***እንኪያ በምን ተጠመቃችሁ? አላቸው። እርሱም፦ በዮሐንስ ጥምቀት አሉት።***
> ***ጳውሎስም፦ ዮሐንስስ ከእርሱ በኋላ በሚመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ ያምኑ ዘንድ ለሕዝብ እየተናገረ በንስሐ ጥምቀት አጠመቀ አላቸው።***
> ***ይህንም በሰሙ ጊዜ በጌታ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ፤***
> ***ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው በልሳኖችም ተናገሩ፥ ትንቢትም ተናገሩ። (የሐሥ 19፡1-6)***

እንደገና በድጋሚ፣ ከበዓለ ሃንሳ ጋር የሚጎዳኝ ክስተት እንመለከታለን፡፡ በኢየሱስ ስም ከተጠመቁ በኋላ፣ በሰዎቹ ላይ መንፈስ ቅዱስ መጣ፣ በልሳኖችም ተናገሩ ትንቢትም ተናገሩ፡፡

በዚህ ምንባብ፣ ከይሁዳና ከሰማርያ ሩቅ በሆነችው በትንሺ በምትገኝ ትልቅ ከተማ በኤፌሶን ስለ ፈሰሰው የመንፈስ ቅዱስ አስደናቂ መገለጫ ሉቃስ ዘግቧል፡፡ የመንፈሱ ሥራ ከኢየሩሳሌም ወደ ሰማርያ ከዚያም ወደ አህዛብ መዳረሱን ሉቃስ ማመልከቱን አስተውለናል፡፡ በዚህ ስፍራ ያልተለመደው ነገር መንፈሱን የተቀበሉት የዮሐንስ መጥምቁ ተከታዮች የነበሩት ናቸው፡፡ የሚገመተው፣ እነዚህኞቹ ዮሐንስ ኢየሱስ ሲጠበቅ የኖረው መሲህ መሆኑን ከመግለጡ አስቀድሞ የዮሐንስን ምስክርነት ሰምተው ንስሓ የገቡ አይሁድ ሳይሆኑ እንደማይቀሩ ነው፡፡

ሉቃስ ይህንን ወቅት ያሰመረበት ምክንያት ሉቃስ በመግቢያው ላይ አንስቶት ለነበረው ጉዳይ እልባት ለመስጠት ነው፡፡ ያም በመጥምቁ ዮሐንስና በኢየሱስ መካከል የነበረው ግንኙነት ነው፡፡ ያንንም በሐሥ 1፡5 ታገኙታላችሁ፡፡ ኢየሱስ የእርሱን አገልግሎት ከመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት ጋር በዚህ መንገድ አነፃፅሮታል፡፡

> ***ዮሐንስ በውኃ አጥምቆ ነበርና፥ እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኃላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ አለ። (የሐሥ 1፡5)***

በኤፌሶን በሚኖሩ የዮሐንስ ደቀመዛሙርት ላይ የመንፈሱ መፍስ ታሪክ መንፈሱን የማምጣቱ የኢየሱስ ሥራ ወደ አዲስ እርከን የተሸጋገረ መሆኑን ያመለክታል፡፡ የዮሐንስ ደቀመዛሙርት እንኳን ሳይቀሩ የክርስቶስ ተከታዮች ሆነዋል የክርስቶስንም መንፈስ ተቀብለዋል፡፡ ክርስቶስን በሙላት መቀበልና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መኖር ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር መስማማት ነው፡፡

ሐዋርያት የቤተክርስቲያንን ተልዕኮ ሲያስፋፉ፣ ድንበር ዘለል የመንግሥቱ አገልግሎታቸው በመንፈስ ቅዱስ ተዓምራዊ መፍሰስ ይረጋገጥ እንደነበር ሉቃስ ግልፅ ያደርግልናል፡፡ በመንፈሱ ኃይል፣ ወንጌል ከኢየሩሳሌም ወጥቶ፣ ወደ ይሁዳ፣ ወደ ሰማርያና ወደ ምድር ዳርቻ ሁሉ ማንም ሳይገታው ይስፋፋ ነበር፡፡ ዛሬም ቢሆን፣ ቤተክርስቲያን የምትለወጥበትና ወንጌልን በተሳካ መንገድ የምታደርስበት ብቸኛ መንገዱ የመንፈስ ቅዱስ

ኃይል ነው፡፡ የወንጌሉ መልእክት ውጤታማና እነተኛ ምስክሮች መሆን የምንፈልግ ከሆነ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መደገፍን በብርቱ ልንሻ ይገባናል፡፡

# 3. ሐዋርያት

የመንፈስ ቅዱስን ድርሻ ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ሁለተኛውን ሐዋርያት የተሰኘውን ርዕሳችንን እንዳስሳለን፡፡ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ከመመለሱ በፊት፣ ሐዋርያቱ ከኢየሩሳሌም አንስተው እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ መንግሥቱን በማስፋት አገልግሎቱን እንዲቀጥሉ ሾሟቸዋል፡፡ መንፈስ ቅዱስ በቀደመችው ቤተክርስቲያን ውስጥ የነበረውን ወሳኝ ድርሻ፣ ሐሥ 1፡8 እንዴት እንደገለጠው ቀደም ብለን ተመልክተናል፡፡ ኢየሱስ ለሐዋርያቱ የተናገረውን እንደገና አድምጡ፡

> ***ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ። (የሐሥ 1፡8)***

በትምህርታችን በዚህኛው ነጥብ ላይ፣ በዚህ ጥቅስ ውስጥ ጎልቶ በሚታየው ሁለተኛ ጉዳይ የሐዋርያት ሃላፊነት ላይ እናተኩራለን፡፡ ኢየሱስ በዚህ ስፍራ እንዳስቀመጠው፣ በዓለም ሁሉ የእርሱ ምስክሮች ይሆኑ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት ተሰጥቷል፡፡

በቀደመችው ቤተክርስቲያን ውስጥ፣ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ የወንጌሉ ምስክሮች የሆኑት “ሰማዕታት” ወይም “ምስክሮች” በመባል ይታወቁ ነበር፡፡ እጅግ በከፋ ሁኔታ፣ ምስክሮቹ ስለ ክርስቶስ በመመስከራቸው ተገርፈዋል ወይን ተገድለዋል፡፡ እንዲያውም፣ የቤተክርስቲያን ትውፊት እንደሚነግረን አብዛኞቹ ሐዋርያት በዚህ መንገድ ሞተዋል፡፡ በተቃውሞ መካከል የክርስቶስ ምስክር የመሆን ይህ መሪ ሃሳብ ሉቃስ ስለ ቀደመችው ቤተክርስቲያን ሲፅፍ ገዢ የሆነው ሃሳብ ነበር፡፡ በዚህ ረገድ፣ ብርቱና ውጤታማ የክርስቶስ ምስክሮች ከመሆን አንፃር ከሐዋርያት የሚልቅ አይገኝም፡፡

የክርስቶስ ምስክር ከመሆን አንፃር ሐዋርያት የነበራቸውን ሃላፊነት በሦስቱ ገፅታዎች ላይ በማትኮር እንመለከተዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ምስክርነታቸው ልዩ መሆኑን እናያለን፡፡ ሁለተኛ፣ በሥልጣን ያከናወኑት እንደነበር እንመለከታለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ የምስክርነታቸውን የተለያየ ተፈጥሮ ማለትም የወንጌልን መልእክት ለማቅረብ የሚጠቀሙበትን የተለያየ ዘዴ እንቃኛለን፡፡ ሐዋርያት ለቢሮው ብቁ የሚያደርጋቸውን ልዩ መመዘኛ በመመልከት እንጀምር፡፡

## ልዩ

ሐዋርያት ቢያንስ በሁለት ምክንያቶች ልዩ ነበሩ፡፡ ለመጀመር ያህል፣ ለቢሮው የተቀመጠው መመዘኛ ማንም ሰው ሐዋርያ ተብሎ ሊጠራ የሚችል እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡

### *መመዘኛዎች*

ከዐሥራ ሁለቱ ቀደምት ሐዋርያት አንዱ የሆነው፣ የአስቆሮቱ ይሁዳ ተብሎ የሚጠራው ሰው፣ ኢየሱስን ለሚሰቅሉት አሳልፎ ሰጠው፡፡ በኋላ ደግሞ፣ ይሁዳ ራሱን አጠፋ፣ ሐዋርያትም ዐሥራ አንድ ብቻ

ሆኑ፡፡ከዚያም፣ ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ፣ የዐሥራ አንዱ ተቀዳሚ ተግባር ይሁዳን የሚተካ ዐሥራ ሁለተኛ ሰው መምረጥ ነበር፡፡

በሐሥ 1፡21-26 ውስጥ፣ የአዲሱን ሐዋርያ መመዘኛዎች ጴጥሮስ በዚህ መንገድ ገልፆታል፡

***ስለዚህ ከዮሐንስ ጥምቀት ጀምሮ ከእኛ ዘንድ እስካረገበት ቀን ድረስ፥ ጌታ ኢየሱስ በእኛ መካከል በገባበትና በወጣበት ዘመን ሁሉ ከእኛ ጋር አብረው ከነበሩት ሰዎች፥ ከእነዚህ አንዱ ከእኛ ጋር የትንሣኤው ምስክር ይሆን ዘንድ ይገባል።***
***ኢዮስጦስም የሚሉትን በርስያን የተባለውን ዮሴፍንና ማትያስን ሁለቱን አቆሙ። ሲጸልዩም። የሁሉን ልብ የምታውቅ አንተ ጌታ ሆይ፥ ይሁዳ ወደ ገዛ ራሱ ስፍራ ይሄድ ዘንድ በተዋት በዚህች አገልግሎትና ሐዋርያነት ስፍራን እንዲቀበል የመረጥኸውን ከእነዚህ ከሁለቱ አንዱን ሹመው አሉ።***
***ዕጣም ተጣጣሉላቸው፥ ዕጣውም ለማትያስ ወደቀና ከአሥራ አንዱ ሐዋርያት ጋር ተቈጠረ። (የሐሥ 1፡21-26)***

እነዚህ ጥቅሶች የሐዋርያትን ቢሮ መመዘኛዎች ይደነግጋሉ፣ ሁሉም በቅዱሳት መጻሕፍት ለተገለጡት ብቻ የሚሠሩ ልዩ መመዘኛዎች ነበሩ፡፡ በመጀመሪያ፣ ከኢየሱስ በቀጥታ የተማሩ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ሁለተኛ፣ ኢየሱስን ከትንሣኤው በኋላ ያዩት ሊሆኑ ይገባል፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ ለቢሮው የሚሾሙት በቀጥታ በእግዚአብሔር ሊሆን ይገባል፡፡ ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት በጠቅላላ እነዚህን ያሟላሉ ምክንያቱም በኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎት ወቅትከኢየሱስ ተምረዋል፣ ከትንሣኤው በኋላ አይተውታል ደግሞም በኢየሱስ በራሱ ተሹመዋል፡፡

ማትያስም እነዚህን መመዘኛዎች ያሟላል ምክንያቱም በምድራዊ አገልግሎቱ ወቅት ከኢየሱስ ተምሯል፣ የተነሣውን ክርስቶስን አይቶታል ደግሞም ዕጣ በመጣል በቀጥታ በእግዚአብሔር ተመርጧል፡፡

ከማትያስ በኋላ፣ በቅዱሳት መጻሕፍት ለሐዋርያነት ቢሮ ተሾሞ የምናገኘው ሰው አንድ ብቻ ነው፡፡ ጳውሎስ፡፡ ጳውሎስ ሐዋርያ ሆኖ የተመረጠው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ነው፡፡ ስለዚህ ቤተክርስቲያን በመጀመሪያዎቹ አካባቢ ስለ እርሱ ሹመት በጥርጣሬ ውስጥ ነበረች፡፡ እርሱ በእርግጥም ከትንሣኤው በኋላ ኢየሱስን እንዳየና ከእርሱም እንደተማረ ደግሞም በኢየሱስ በራሱ እንደተሾመ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስተምሩናል፡፡

ለምሳሌ፣ ሉቃስ በሐሥ 9፡3-6 እንደዘገበው፣ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ ላይ ከሞት ከተነሣው ጌታ ጋር ተገናኝቷል፡፡ በተጨማሪም፣ በሐሥ9፡15 እና 22፡12-16 እንደምናነበበው በእግዚአብሔር በራሱ ለቢሮው ተሹሟል፡፡ በእርግጥም፣ በሐሥ 9፣22 እና 26 ውስጥም እውነተኛ ሐዋርያ መሆኑን ለማስረገጥ ሉቃስ የጳውሎስን ሹመት ሦስት ጊዜ ጠቅሶታል፡፡

ግን ጳውሎስ ራሱም እንኳን ኢየሱስ እስኪያርግና ከዚያም በኋላ እስከተለወጠበት ቀን ድረስ ወደ እምነት እስካልመጣ ድረስ  የእርሱ መመዘኛዎች ያልተለመዱ መሆኑን ተቀብሏል፡፡ ጳውሎስ የእርሱን ልዩ ሐዋርያነት በ1ኛ ቆሮ 15፡8-9 ጠቅሶታል፡

***ከሁሉም በኋላ እንደ ጭንጋፍ ለምሆን ለእኔ ደግሞ ታየኝ።***
***እኔ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ ነኝና፥ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ስላሳደድሁ ሐዋርያ***

*ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ፤ (1ኛ ቆሮ 15፡8-9)*

**የምሥረታ ወቅት**

እነዚህን የተለዩ መመዘኛዎች ከማሟላት ባሻገር፣ በቤተክርስቲያን የምሥረታ ሕይወት ውስጥ በማገልገላቸው ሐዋርያት ልዩ ናቸው፡፡ በዚህ ልዩ ወቅት፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ቤተክርስቲያን ለመመሥረቱ ሃላፊነት ተሾሙ፡፡ ሥራቸውንም በአግባቡ ከመሥራታቸው የተነሣ እና ቤተክርስቲያንም በመሠረቱ ላይ በመቆሟ ምክንያት የእነርሱ ልዩ ሥራ አስፈላጊ አልሆነም፡፡

ሐዋርያት የቤተክርስቲያን መሠረት የመሆንን አገልግሎት እንደሰጡ ሉቃስ በብዙ መንገድ ጠቅሶታል፡፡ ቀደም ባለው ትምህርት እንደተመለከትነው፣ ሐዋርያት ወንጌልን በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳ፣ በሰማርያ እና በምድር ዳር ሁሉ ለማድረስ ተቀዳሚ ምስክሮች ሆነዋል፡፡ በወንጌል አገልግሎታቸው፣ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ከይሁዲነት፣ ከረከሰው የሳምራውያን አምልኮ እና ከአህዛብ ጣዖት አምላኪነት አምልጠዋል፡፡ በአመራራቸውም፣ በታሪክ ውስጥ የመጀመሪዋ ቤተክርስቲያን ተመሠረተች እናም ቤተክርስቲያን የምትከተለውም መስመር ተዘረጋ፡፡ በእነዚህና በበርካታ ሌሎች መንገዶች፣ ሐዋርያት ልዩ ሥራ በልዩ ወቅት አከናወኑ፡፡ እነዚህ ጊዜያት ተመልሰው አይመጡም ይህም ሥራ እንደገና ሊሠራ አይገባውም፡፡

በሐሥ 2፡19-20 ውስጥ፣ የሐዋርያትን ልዩ የምሥረታ ሥራ ጳውሎስ በዚህ መንገድ አጠቃልሎታል፡

***እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም። በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፥ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ (የሐሥ 2፡19-20)***

ሌላ የማዕዘን ድንጋይ፣ ሌላ ኢየሱስ ሊኖር አይችልም፡፡ በተመሳሳይም መንገድ፣ ሌላ መሠረት፣ የቤተክርስቲያን መሠረት ሆኖ የሚያገለግል ሌላ ሐዋርያና ነቢይ ሊኖር አይችልም፡፡

የሚያሳዝነው ግን፣ በእኛ ዘመን አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት በመካከላቸው የሚያገለግሉ ባለሥልጣን ሐዋርያት እንዳሏቸው ይናገራሉ፡፡ ሆኖም፣ የመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት የቢሮውን መመዘኛ በተለየ መንገድ ያሟሉ፣ ለየት ላለ የምሥረታ ወቅትም የተሾሙ እና ያም ጨርሶ ሊደገም የሚችል እንዳልሆነ ሉቃስ በግልፅ አስቀምጦታል፡፡ የሐዋርያትም ምስክርነት በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ተሰብስቦ ተቀምጦልናል፣ ስለዚህ እነዚያም የመሰሉ ሐዋርያት በዛሬዋ ቤተክርስቲያን ውስጥ ልንጠብቅ አይገባንም፡፡

## ሥልጣን የተቀበሉ

ሐዋርያት ለየት ባለ መንገድ ስለ ኢየሱስ የመሰከሩ መሆኑን ከተመለከትን፣ ምስክርነታቸው በሥልጣን የነበረ መሆኑን ለመመልከት እንዘጋጃለን፡፡ የሐዋርያት ሥልጣን በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በበርካታ መንገዶች ታይቷል፣ ነገሩን በቀላሉ ለማስረዳት ግን ከእነዚያ ውስጥ በአራቱ ላይ ብቻ እናተኩራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ የሐዋርያት ሥልጣን በቢሮአቸው ተግባር ውስጥ ይታያል፡፡ ሁለተኛ፣ በአገልግሎታቸው እግዚአብሔር በገለጠው በረከት ታይቷል፡፡ ሦስተኛ፣ ተዓምራትን በማድረጋቸው ኃይል ውስጥ ተረጋግጧል፡፡ አራተኛ ደግሞ፣ መቀበል በቀጠሉት ራእይ ውስጥም በግልፅ ይታያል፡፡ አስቀድመን ሥልጣናቸውን በሚገልፀው የቢሮአቸው ተግባር እንጀምር፡፡

**ተግባር**

"ሐዋርያ" ወይንም በግሪኩ አፖስቶሎስ የሚለው ቃል፣ መሠረታዊ ፍቺው የተላከ ማለት ነው፡፡ በተለምዶ አገልግሎት ላይ የሚውለው ለመልእክተኛ፣ አንድን ተልዕኮ ለመፈፀም ለተላኩ ወኪሎች እና በላኳቸው ምትክ እንዲናገሩ ሥልጣን የተሰጣቸውን አምባሳደሮች ነው፡፡ ለምሳሌ፣ በሉቃስ 10 ውስጥ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እንዲሰብኩ ኢየሱስ ሰባ-ሁለቱን ሲልክ፣ በዚያን ወቅት የክርስቶስን ሥልጣን የተሸከሙ፣ ወቅታዊ አምባሳደሮች ነበሩ ማለት ነው፡፡

በሉቃስ 10፡16 ውስጥ፣ ኢየሱስ ሚሲዮናውያንን እንዲህ ሲል ልኳቸዋል፡

> ***የሚሰማችሁ እኔን ይሰማል፥ እናንተንም የጣለ እኔን ይጥላል፤ እኔንም የጣለ የላከኝን ይጥላል። (ሉቃስ 10፡16)***

በዚህ ስፍራ ሚሲዮናውያኑ እንደ ክርስቶስምትኮች እንዲታዩ እንደሚጠበቅ እናያለን፡፡ ሚሲዮናውያንን የተቀበሉ ኢየሱስን እንደተቀበሉ፣ ክርስቶስን የተቀበሉ ደግሞ የላከውን ማለትም አብን እንደተቀበሉ ይቆጠራሉ፡፡

ከዚህም ባሻገር፣ በሉቃስ 10፡17-19 ሚሲዮናውያኑ ተመልሰው ሲመጡ የተደረገውን ውይይት አድምጡ፡

> ***ሰብዓውም በደስታ ተመልሰው። ጌታ ሆይ፥ አጋንንት ስንኳ በስምህ ተገዝተውልናል አሉት።***
> ***እንዲህም አላቸው ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ።***
> ***እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፥ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፥ የሚጐዳችሁም ምንም የለም። (ሉቃስ 10፡17-19)***

የእርሱ ሚሲዮናውያን እንዲሆኑ ሲሾማቸው፣ ለሰባ ሁለቱ ከሥልጣኑ አካፈላቸው፡፡ ስለዚህ፣ እርሱን የመወከላቸው ነገር ተምሳሊታዊ ብቻ አልነበረም፡፡ ይልቁኑ የእርሱ ባለሥልጣን ወኪሎች ነበሩ፡፡ የማይሻሩ መምህራን አልነበሩም፣ ግን አጋንንትን የሚስወጡበት እና የመንግሥቱን መምጣት የሚያውጁበት ሥልጣን ነበራቸው፡፡

ከዚህ ጋር በሚመሳሰል መንገድ፣ ሐዋርያት ሥልጣን የተቀበሉ አምባሳደሮች ነበሩ፡፡ ሆኖም በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ክርስቶስን የመወከላቸው ነገር በሁለት ዋና መንገዶች ከሌሎቹ ደቀመዛሙርት የተለየ ነበር፡፡ በመጀመሪያ፣ ሐዋርያት የተቀበሉት ወንጌልን የማስፋፋቱን ተልዕኮ ብቻ እንዳልነበርና በቤተክርስቲያንም ዘላቂነት ባለው ቢሮ እንዲያገለግሉ ተሹመዋል፡፡ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ሐዋርያት በማንም ሰው ወይም ቢሮ አይተኩም፡፡ ለተወሰነ ጊዜ ሳይሆን፣ በዘላቂነት የክርስቶስን ሥልጣን እንዲይዙ ተሹመዋል፡፡ ሁለተኛ፣ ሐዋርያት የክርስቶስን ቤተክርስቲያን አመሠራረትም ሆነ አስተዳደር በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ እንዲናገሩ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ በሐሥ 15 የኢየሩሳሌም ጉባኤ ዘገባ እንደሚያመለክተን፣ የሐዋርያት ቃል በቤተክርስቲያን ውስጥ ተቀባይነት እንዲኖረው ተደርጓል፡፡ የሚያስተላልፏቸው የትኞቹም ውሳኔዎች እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሰው ሊቀበላቸው ይገባል፡፡ በ2ኛ ጴጥሮስ 3፡2 ውስጥ ሐዋርያዊ ሥልጣንን ጴጥሮስ ገለጠበትን መንገድ አድምጡ፡

***… በሐዋርያቶቻችሁም ያገኛችኋትን የጌታንና የመድኃኒትን ትእዛዝ እንድታስቡ በሁለቱ እያሳሰብኋችሁ… (2ኛ ጴጥ 3፡2)***

በዚህ ስፍራ ጴጥሮስ እንዳመለከተው፣ የኢየሱስ ፈቃድና አስተምህሮ ታማኝ ባለአደራዎች በመሆናቸው ምክንያት ተቀባይነት ይኖራቸዋል፡፡

የሐዋርያትን ተግባር ከገለፅን፣ በወንጌሉ መስፋፋት አማካይነት የእነርሱን የተለየ አገልግሎት እግዚአብሔር የባረከበትን መንገድ ወደመመልከቱ እንሸጋገራለን፡፡

## በረከት

በሐዋርያት ሥራ ውስጥ፣ ሐዋርያት ወንጌልን በሰበኩበት ወቅት ሁሉ አዳዲስ አማኞችን በመጨመር እግዚአብሔር ይባርካቸው ነበር፡፡ እንደተመለከትነው፣ በበዓለ ሃምሳ ዕለት ጴጥሮስ የሰበከው ስብከት ቤተክርስቲያንን ከ 120 ወደ 3000 አባላት አሳድጓታል፡፡ ይህን መሰሉ በረከትም በሐዋርያት ሥራ በጠቅላላ ቀጥሏል፡፡

እንደ ጸሐፊ፣ ሉቃስም ይህ ውጫዊ፣ የቁጥር የቤተክርስቲያን እድገት የእግዚአብሔር ይሁንታና ኃይል ማረጋገጫ እንደሆነ አንባቢዎቹ እንዲረዱለት በጥንቃቄ ያስተምራል፡፡ ይህን ያደረገበት አንዱ መንገድም የእውቁን ፈሪሳዊ የገማልያልን ንግግር መጥቀስ ነው፡፡

በሐሥ 5፡38-39፣ ገማልያል በሸንጎው ፊት ስለ ሐዋርያት እንዲህ ተናግሯል፡

> ***አሁንም እላችኋለሁ። ከእነዚህ ሰዎች ተለዩ ተዉአቸውም፤ ይህ አሳብ ወይም ይህ ሥራ ከሰው እንደ ሆነ ይጠፋልና፤***
> ***ከእግዚአብሔር እንደ ሆነ ግን ታጠፉአቸው ዘንድ አይቻላችሁም፥ በእርግጥ ከእግዚአብሔር ጋር ስትጣሉ ምናልባት እንዳትገኙ። (የሐሥ 5፡38-39)***

ከዚህ አመለካከት አንፃር ሲታይ፣ በሐዋርያት ሥራ ጠቅላላ መጽሐፍ ውስጥ የሐዋርያት የተባረከ የወንጌል አገልግሎት መንፈስ ቅዱስ አገልግሎታቸውን በኃይል የሞላና ማረጋገጫ የሰጠበት መሆኑን ያስረዳል፡፡

ከተግባራቸውና እግዚአብሔር በወንጌል አገልግሎታቸው ከሰጣቸው የቁጥር እድገት በረከት ባሻገር፣ የሐዋርያት ሥልጣን አገልግሎታቸውን ባጀበው ጠዓምራትም ውስጥ ተገልጧል፡፡

## ተዓምራት

በጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ የተዓምራት አንዱ ተግባር የእግዚአብሔር መልእክተኛ የሚናገረው እውነት መሆኑንና የእግዚአብሔርንም ሥልጣን የተሸከመ መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡ በዘፀአት መጽሐፍ፣ ሙሴ የእውነተኛው አምላክ መልእክተኛ መሆኑን በፈርዖን ፊት ለማረጋገጥ በርካታ ተዓምራትን አድርጓል፡፡ በ1ኛ እና በ2ኛ ነገሥት መጽሐፍት ውስጥ ኤልያስና ኤልሳዕም ትንቢቶቻቸውና ትምህርቶቻቸው ከእግዚአብሔር መሆኑን ለማረጋገጥ ተዓምራትን አድርገዋል፡፡ በወንጌላትም ውስጥ፣ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የተቀባው የእግዚአብሔር አገልጋይ እና ነቢይ ህዝቡን ሊያድንና ሊገዛ የተላከ መሆኑን ለማረጋገጥ ተዓምራትን አድርጓል፡፡

በተመሳሳይም መንገድ፣ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በሐዋርያት  የተገለጡት ተዓምራት ስለ ክርስቶስ የሚያቀርቡት ምስክርነት እውነት መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ በሐሥ 5፡16 ሐዋርያት የታመመ ፈውሰዋል፡፡ በሐሥ 14፡8 ሽባው ወደ ጤንነቱ ተመልሷል፡፡ በሐሥ 9፡40 የሞተ አስነስተዋል፡፡ በሐሥ 13፡11 ክፉውን ሰው መቅሰፍት ጠርተውበታል፡፡ በሐሥ 12፡10 ከእስር አምልጠዋል፡፡ በሐሥ 27፡44 ከመርከብ ስብራት ተርፈዋል፡፡ በሐሥ 28፡3 ከመርዛማ እባብ ተርፈዋል፡፡ እንዲያውም፣ እንደ ሐሥ 5፡15 አባባል ኃይላቸው እጅግ ታላቅ ስለነበር፣ የጴጥሮስ ጥላ እንኳን የነካውን ሰው ሁሉ ይፈውስ ነበር፡፡ እንደ ሐሥ 19፡11-12 አባባል፣ ከጳውሎስ ተወሰደ ጨርቅ ሁሉ ኢጋንንትን ያስወጣ ደዌንም ይፈውስ ነበር፡፡ እነዚህም የመሰሉ ኃይለኛ ተዓምሮች ከእግዚአብሔር ብቻ የሚመጡ፣ ሐዋርያት የእርሱ ባለስልጣን ምስክሮችች መሆናቸውን የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡

ለዚህም ነው ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮ 12፡12 በእርሱ የተገለጠውን ተዓምራት እንዲህ የገለጠው፡

> ***በእርግጥ የሐዋርያነት ምልክት በመካከላችሁ በምልክትና በድንቅ ነገር በተአምራትም በሁሉ ትዕግሥት ተደረገ። (ሐሥ 12፡12)***

በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የታጀቡ ተዓምራዊ ሥራዎች የሐዋርያ መለያዎች ናቸው፣ ማለትም ስለ ክርስቶስ እና ስለ ሥራው በታማኝነት የሚመሰክር የመሆኑ ማረጋገጫ ነው፡፡

የሐዋርያትን ተግባር፣ በእነርሱ አማካይነት ለተሰበከው የወንጌል ስብከት እግዚአብሔር የሰጠውን በረከት እና ተዓምራቶቻቸውን ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ የተቀበሉት ራእይ እንዴት ሥልጣናቸውን እንዳረጋገጠ እንመለከታለን፡፡

## ራእይ

መንፈስ ቅዱስ ሐዋርያትን ይመራቸው እንደነበር፣ የወንጌልን እውነት በገሃድ እንዲገለጥ እንዲያደርጉ ያግዛቸው እንደነበር፣ ለቤተክርስቲያን በጠቅላላ የሚጠቅም ውሳኔ እንዲወስኑ ያስቻላቸው እንደነበር፣ ቤተክርስቲያን ወደ ብስለት ማደግ የምትችልባቸውን ውቅረ-ነገሮች ለማዋቀር ይረዳቸው እንደነበር ሉቃስ ደጋግሞ ዘግቧል፡፡ ለምሳሌ፣ በሐሥ 10፣ አህዛብ ወደ ይሁዲነት ቀድመው ሙሉ በሙሉ መግባት ሳይጠበቅባቸው ወደ ቤተክርስቲያን እንዲያመጣቸው ለማስተማር ጴጥሮስ ከእግዚአብሔር ራእይ ተቀብሏል፡፡ በሐሥ 16 ደግሞ፣ የመንግሥቱን ወንጌል በብዙ ለማስፋፋት ያስችል ዘንድ፣ ወንጌልን በመቄዶኒያ እንዲሰብክ ጳውሎስ ራእይ ተቀብሏል፡፡

ለሉቃስ የመጀመሪያ ተደራሲያን እና ለተቀሩትም የቀደመችው ቤተክርስቲያን አባላት፣ የሐዋርያት ይፋ ተግባር፣ በአገልግሎት መባረካቸው፣ ሥልጣን የተሞሉት ተዓምራት እና ራእይ የማይጠየቀው ሥልጣናቸው አሳማኝ ማስረጃዎች ናቸው፡፡ ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ እንደዘገበው፣ የቀደመችውም ቤተክርስቲያን ትምህርታቸውንና ፍርዳቸውን በመቀበል ለሐዋርያት ባለሥልጣናዊ ምስክርነት እና አመራር በጎ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በተመሳሳይም መንገድ፣  የዘመናችንም ክርስቲያኖችም ትምህርቶቻቸው ጠቅለል ብለው ለቀረቡባቸው ለምሳሌ እንደ ሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ላሉት እና በአዲስ ኪዳን ለሰፈሩት ሥልጣናዊ ጽሁፎች ራሳችንን በመስጠት፣ ለእነዚህ የክርስቶስ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደሮች ራሳቸውን ሊያስገዙ ይገባቸዋል፡፡

የሐዋርያትን ባለሥልጣን እና ልዩ ምስክርነት በልቡናችን ይዘን፣ እነርሱና ተከታዮቻቸው ለዓለም የክርስቶስ ወንጌል ምስክሮች የሆኑባቸውን የተለያዩ መንገዶች ወደ መመልከቱ እንሸጋገራለን፡፡

## የተለያዩ

ሐዋርያትና ተከታዮቻቸው ስለ ክርስቶስ የመሰከሩባቸውን በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ መንገዶች አስመልክቶ የምናደርገው ውይይት በሁለት ይከፈላል፡፡ በመጀመሪያ፣ ስለ ክርስቶስ ለመመስከር የተጠቀሙባቸውን የተለያዩ ስልቶች እንዳስሳለን፡፡ ሁለተኛ፣ ይህንን መስክርነት የሠጡባቸውን የተለያዩ መቼቶች እንጠቅሳለን፡፡ አስቀድመን በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የተጠቀሱትን የተለያዩ ስልቶች እንመልከት፡፡

## ስልቶች

ሐዋርያትና ተከታዮቻቸው ስለ ክርስቶስ ለዓለም ለመመስከር የተጠቀሙባቸውን የተለያዩ ዘዴዎች የምንጠቅስባቸው በርካታ መንገዶች ቢኖሩም፣ ስለ ስድስቱ ተቀዳሚ አቅራቦቶች ማሰባችን ጠቃሚ ነው፡፡ በመጀመሪያ፣ ደጋግመው ታሪክን ያጣቅሳሉ፣ በተለይም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ህይወት፣ ሞትና ትንሣኤ በመላው የሮማ ግዛት የተዘገቡትን ከታሪክ ማጣቀስን ይመርጣሉ፡፡

ለምሳሌ፣ በሐሥ 26፡26፣ ጳውሎስ ለንጉሥ አግሪጳ እንዲህ ተናግሯል፡

> ***በእርሱ ፊት ደግሞ በግልጥ የምናገረው ንጉሥ ይህን ነገር ያውቃል፤ ከዚህ ነገር አንዳች እንዳይሰወርበት ተረድቼአለሁና፤ ይህ በስውር የተደረገ አይደለምና። (የሐሥ 26፡26)***

በዚህ ምንባብ፣ የጳውሎስ ዋና ነጥብ እርሱና ቤተክርስቲያን ሲያውጇቸው የነበሩ መሠረታዊ እውነታዎች በጥንታዊው ዓለም የታወቁ እንደነበሩ ማመልከት ነው፡፡ ይህን የመሰሉ ታሪካዊ እውነታዎችን መጥቀስ ሐዋርያት ለማያምኑት በሚመሰክሩበት ወቅት ይጠቀሙበት የነበረ የተለመደ ስልት ነበር፡፡

ሁለተኛ፣ ሐዋርያት የወንጌል መልእክታቸውን ለማረጋገጥ የቅዱሳት መጻሕፍት እውነቶችን ዘወትር ያጣቅሱ ነበር፡፡ ለአይሁድ ተደራሲያን ሲመሰክሩ፣ ሐዋርያት ደጋግመው ከብሉይ ኪዳን ይጠቅሱ ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ በሐሥ 3፡22፣ ኢየሱስ ለዘመናት ሲጠበቅ የነበረው መሲህ መሆኑን ለአይሁድ ለማረጋገጥ ሲል ጴጥሮስ የሙሴን ንግግሮች ጠቅሷል፡፡ በሐሥ 23፡6 ደግሞ፣ ስለ ሙታን ትንሣኤ ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተወሰደውን እና አይሁድ የሚያምኑትን ጳውሎስ ጠቅሶታል፡፡

ሦስተኛ፣ ሐዋርያት ለአህዛብ ተደራሲያን ሲመሰክሩ፣ በአምላክ የለሾቹ ሥርዓት ውስጥ የሚገኙትን እውነተኛ የእምነት አቋሞች እና እግዚአብሔር በፍጥረቱ ውስጥ ያስቀመጠውን መገለጥ ይጠቅሱ ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ በሐሥ 17፡24-27 ውስጥ፣ ጳውሎስ በአቴና የወንጌል አገልግሎቱን ሊሰጥ ሲጀምር ለመነሻ የጠቀሰው የተለመደውን የአረማውያን አመለካከት ነው፡፡

> ***ዓለሙንና በእርሱ ያለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነውና እጅ በሠራው መቅደስ አይኖርም፤***
> ***እርሱም ሕይወትንና እስትንፋስን ሁሉንም ለሁሉ ይሰጣልና አንዳች እንደሚጎድለው በሰው እጅ አይገለገልም።***
> ***ምናልባትም እየመረመሩ ያገኙት እንደ ሆነ፥ እግዚአብሔርን ይፈልጉ ዘንድ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ የሰውን ወገኖች ሁሉ ከአንድ ፈጠረ፥ የተወሰኑትንም ዘመኖችና ለሚኖሩበት ስፍራ ዳርቻ መደበላቸው። ቢሆንም ከእያንዳንዳችን የራቀ አይደለም። (ሐሥ 17፡24-27)***

ጳውሎስ ያቀረበው የአመለካከት ነጥብ በክርስቲያኖችና በአይሁድ ብቻ የሚታወቁ ሳይሆኑ በብዙ አረማውያንም ጭምር ነበር፡፡ እንዲያውም፣ በተመሳሳይ አድራሻ በአቴንሱ በአርዮስ ፋጎስ፣ ጳውሎስ የአረማውያንን ስነ-ጽሑፍ ጠቅሷል፡፡ በሐሥ 17፡28 የተናገረውን አድምጡ፡

> **ከእናንተ ከባለ ቅኔዎች አንዳንዶች ደግሞ። እኛ ደግሞ ዘመዶቹ ነንና ብለው እንደ ተናገሩ፥ በእርሱ ሕያዋን ነንና እንንቀሳቀሳለን እንኖርማለን። (የሐሥ 17፡28)**

በዚህ ስፍራ ጳውሎስ በአቴና ስለ ክርስቶስ ሲመሰክር ስለ ክርስትና ሚነሳውን ጉዳይ ለማስረገጥ የግሪክን ግጥም ጠቅሷል፡፡

አራተኛ፣ ሐዋርያት ክርስቶስን ለሌሎች ሲያቀርቡ የግል ልምምዳቸውን ጋግመው ያቀርቡ ነበር፡፡ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ፣ ጳውሎ ይህንን የመሰለውን አቀራረብ ይጠቀም እንደነበር ሉቃስ ዘግቧል፡፡ ለምሳሌ፣ ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ ላይ የገጠመውን፣ ሉቃስም በሐሥ 9 የዘገበውን አስደናቂ ልምምድ ይጠቅሳል፡፡ በሐሥ 22፣ ጳውሎስ የቀደመውን ሕይወቱን፣ በኢየሩሳሌም በአይሁድ ህዝብ ፊት፣ በሐሥ 26 ደግሞ ለንጉሥ አግሪጳ ገልጦ ነበር፡፡

አምስተኛ፣ ሐዋርያት የሚሰብኩትን ወንጌል እውነት ለማረጋገጥ በርካታ ምልክቶችንና ድንቆችን ያደርጉ ነበር፡፡ በዚህ ትምህርት ቀደም ብለን እንደተመለከትነው፣ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ሐዋርያት በሚያደርጓቸው ተዓምራት የተሞላ ነው፡፡ ሐዋርያት ተዓምራትን እንዲያደርጉ መንፈስ ቅዱስ ኃይልን ሲሰጣቸው፣ ያንን የሚያደርገው ስለ ክርስቶስ የሚሰጡትን ምስክርነት ለመደገፍ ነበር፡፡

ስድስተኛ፣ ሐዋርያት ለክርስቶስ በነበራቸው ጽኑ ፍቅር አማካይነት ይመሰክሩ ነበር፡፡ የሚያገኟትን ጥቂት ትኩረት ወደ ክርስቶስ ለማመልከት ይጠቀሙባት ነበር፣ ደግሞም በመከራ ውስጥ እያለፉም ሆነ እየተፈተኑም ጥሪውን ቸል ማለትን አሻፈረኝ ብለው ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ በሐሥ ምዕራፍ 14 በልስጥራን የሚኖሩ ሰዎች ጳውሎስና በርናባስን ሊያመልኩ ሲሞክሩ፣ ጳውሎስ እርሱ እንደ እነርሱ ሰው መሆኑን በመናገር ህዝቡን ወደ እግዚአብሔር መርቷል፡፡ በሐሥ 4 ውስጥ ደግሞ፣ የአይሁድ ሸንጎ ሐዋርያትን በፍርድ ፊት አቅርቦ ደግመው ወንጌልን እንዳይሰብኩ ሲያዝዛቸው፣ ሐዋርያት ግን ዝም ማለትን አሻፈረኝ አሉ፡፡ በሐሥ 5፡28-29 እንዲህ እናነብባለን፡፡

> ***ሊቀ ካህናቱም። በዚህ ስም እንዳታስተምሩ አጥብቀን አላዘዝናችሁምን? እነሆም፥ ኢየሩሳሌምን በትምህርታችሁ ሞልታችኋል፤ የዚያንም ሰው ደም በእኛ ታመጡብን ዘንድ ታስባላችሁ ብሎ ጠየቃቸው።***
> ***ጴጥሮስና ሐዋርያትም መልሰው አሉ። ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል። (ሐሥ 5፡28-29)***

ሐዋርያት ስለ ወንጌል ሲመሰክሩ የተለያዩ ስልቶችን ይጠቀሙ ነበር፡፡ በምሳሌነታቸውና በአስተምህሯቸውም፣ የቀደመችው ቤተክርስቲያን ያንኑ እንድታደርግ አሰልጥነዋል፡፡ ይህ ሉቃስ የጻፈው የሐዋርያት ሥራ ዘገባ በየዘመናቱ የሚኖሩትን ክርስቲያኖች ሊያበረታታ እና የወንጌል ምስክር ለመሆን ስንነሳ እግዚአብሔር እንድንጠቀምባቸው የሚፈልጋቸው በርካታ ስልቶች እንዳሉ ሊያሳይ ይገባል፡፡

ሐዋርያት ስለ ክርስቶስ ሲመሰክሩ ከተጠቀሙባቸው የተለያዩ ስልቶች በተጓዳኝ፣ ስለ ክርስቶስ የመሰከሩባቸውንም የተለያዩ መቼቶች ልንዳስስ ይገባናል

## መቼቶች

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ሐዋርያት ለወንጌል ምስክርነት የሰጡባቸውን የተለያዩ መቼቶች ልናጠቃልል የምንችልባቸው በርካታ መንገዶች አሉ፡፡ ነገሩን ቀለል ለማድረግ ግን፣ እነዚህን መቼቶች በአራት ጎራዎች እናቧድናቸዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ህዝባዊ ንግግሮች ነበሩ፡፡ በዚህ ወቅት ሐዋርያት በአደባባይ መቼት፣ በስብከት፣ በመከላከያ ንግግር ወይም በሌላ ዓይነት የንግግር ዘይቤ ለበርካታ ህዝብ ንግግር ያደርጉ እንደነበር ልብ ልንል ይገባናል፡፡

በእነዚህ ዓይነት አቀራረቦች፣ ሐዋርያት መልእክት እንደሚያቀርቡለት ተደራሲ ሁኔታ ቃሎቻቸውን በመምረጡ ረገድ ጥንቃቄ ያደርጉ ነበር፡፡ በዚህ ትምህርት እንደተመለከትነው፣ ለአይሁድ በአንድ መንገድ ሲናገሩ፣ ለአህዛብ ደግሞ በሌላ መንገድ ይናገሩ ነበር፡፡

ሁለተኛ፣ ሐዋርያት በሙግት ወይም በክርክር መልክም ይመሰክሩ ነበር፡፡ በዚህ መቼት፣ ሰዎች አፀፋዊ መከራከሪያ እንዲያቀርቡ ይጋበዙ ነበር፣ ሐዋርያት ደግሞ ለወንጌል ጥብቅና ይቆሙ ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ በሐሥ 19፣ ጳውሎስ በጢራኖስ አዳራሽ፣ (የአጻጻፍ ክህሎቶች እና አዳዲስ ሃሳቦች በህዝብ ፊት ይፈተን የነበረበት በኤፌሶን የሚገኝ ስፍራ) ይከራከር ነበር፡፡

ሦስተኛ፣ ሐዋርያትና ይከተሏቸው የነበሩ ሰዎች በየቤቱ እየተዘዋወሩ ይመሰክሩ ነበር፡፡ በጥንታዊው ዓለም፣ አንድ ቤተሰብ ከወላጆችና ከልጆቻቸው ባሻገር ብዙዎችን ያካተተ ነበር፡፡ በርካታ ዘመድ አዝማድ፣ ጓደኞች፣ እና የቤት ሠራተኞችን ይይዝ ነበር፡፡ ስለዚህ፣ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ስለ ቤተሰብ ስናነብብ፣ ቤተዘመድን ማለትም ልጆችን፣ አያቶችን፣ አጎቶችንና አክስቶችን፣ እንዲሁም ሠራተኞችን፣ በበርካታ ወቅቶችም ባሪያዎችንም በምናባችን ማስቀመጥ ይገባናል፡፡ በአማካይ የቤተሰብ አጠቃላይ ቁጥር ከ 15 እስከ 20 ይደርሳል፡፡ ሐዋርያት ለቤተሰብ የሰጡትን ምስክርነት በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በበርካታ ስፍራዎች እናገኛለን፡፡ ለምሳሌ፣ የሐሥ 10፣ ጴጥሮስ ለቆርኔሌዎስ ቤተሰብ፤ በምዕራፍ 16፣ ጳውሎስ ለሊዲያና ለፊልጵስዩሱ ወህኒ ጠባቂ ቤተሰብ መስክረዋል፡፡

አራተኛ፣ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በተጨማሪም የአንድ ለአንድ የወንጌል ምስክርነትን አንዱ የምስክርነት መንገድ አድርጎ ይዞታል፡፡ ለምሳሌ፣ በሐሥ ምዕራፍ 25 ውስጥ፣ ጳውሎስ ቃሎቹን በተለይም ለንጉሥ አግሪጳ እውቀትና ልምድ በሚመጥን መንገድ እንደ ግለሰብ መስክሮለታል፡፡

በአጭሩ፣ ሐዋርያት ምስክርነታቸውን በተወሰኑ መንገዶች ወይም በተወሰኑ መቼቶች ብቻ አልገደቧቸውም ነበር፡፡ የሐዋርያት ሥራን መጽሐፍ ስንዳስስ፣ የተገኘውን ዕድል ሁሉ ሲጠቀሙበት፣ ለእያንዳንዱ ተደራሲ አግባብነት ባለው መንገድ የወንጌልን መልእክት ሲደርሱ እናገኛቸዋለን፡፡ ይህንንም በማድረጋቸው፣ ሐዋርያት ምሳሌነትን ይተዉልናል፣ ከእኛም ተደራሲያን ጋር በእጅጉ የሚስማሙ የወንጌል ውቅረ ነገሮችን አፅንዖት እንድንሰጣቸው አስተምረውናል፡፡ ከዚያም ባሻገር ወንጌል ከማያምኑት ጋር የሚዛመድበትን ልዩ መንገዶች እንድናገኝ ያመለክቱናል፡፡

# 4. ቤተክርስቲያን

መንፈስ ቅዱስና ሐዋርያት የተሰኙትን መሪ ሃሳቦች ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ወደ ሦስተኛው የሐዋርያት ሥራ መሪ ሃሳብ፡ ሐዋርያት ወደ መሠረቷት ቤተክርስቲያን እንሸጋገራለን፡፡

ቤተክርስቲያን የተሰኘውን መሪ ሃሳብ በሁለት መንገዶች እንመረምረዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ የቤተክርስቲያንን አስፈላጊነት እናያለን፡፡ ሁለተኛ፣ ቤተክርስቲያን በሐዋርያት የተጀመረውን ሥራ ለማስቀጠል ያደረገችውን ዝግጅት እንመለከታለን፡፡

## አስፈላጊነት

ሐዋርያቱ ቤተክርስቲያንን እንዲገነቡ ክርስቶስ ላካቸው፡፡ ለምን? በጣት የሚቆጠሩ ሰዎች ብቻ የክርስቶስን መልእክት ወደ ዓለም ሁሉ መውሰድ እንደማይችሉ ሐዋርያት ያውቁ ስለነበር፤ በምድር ሁሉ የመንግሥቱን ወንጌል የሚያውጁ የምስክርነት ዘማቾች ያስፈልጓቸው ነበር፡፡

የሐዋርያትን ተልዕኮ ከግብ ለማድረስ ቤተክርስቲያንን አስፈላጊ የሚያደርጓትን ሁለት ምክንያቶች እንመለከታለን፡፡ በመጀመሪያ፣ የሐዋርያትን አካላዊ ውሱንነት እናያለን፣ ማለትም የተሰጣቸውን ተልዕኮ ብቻቸውን መፈፀም የሚያስችል አካላዊ ብቃት ያልነበራቸው መሆኑ ማለት ነው፡፡ ሁለተኛ፣ በጊዜ የተገደቡ መሆኑን፣ ማለትም የሚኖሩት መደበኛውን የሕይወት ዘመን ልክ ብቻ በመሆኑ ለቀጣዩ ትውልድ መመስከር አይችሉም፡፡ ሐዋርያት አካላዊ ገደብ ያላቸው በመሆኑ እንጀምር፡፡

## አካላዊ ውሱንነት

አስቀድመን እንደተመለከትነው፣ የሐዋርያት ሥራ ወንጌልን በማወጅ የክርስቶስ ምስክር መሆን ነው፡፡ ሆኖም ግን፣ እነርሱ ራሳቸው ብ፣ቻ ለመላው ዓለም "ሕያዋን መልእክቶች" ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ይህንን ችግር ለማቃለል፣ እውነተኛ ምስክር የመሆኑን ኃላፊነት ሐዋርያት ለቤተክርስቲያን ሰጡ፡፡ በሐዋርያት የወንጌል ምስክርነት ሰዎች ሲጨመሩ፣ እነዚያ አማኞች ራሳቸው በራሳቸው ፈቃድ "ሕያዋን መልእክቶች" ይሆኑ ጀመር፡፡ ወንጌልን በመኖር፣ በዚያም ለቤተሰቦቻቸውና ለጎረቤቶቻቸው ስለ ክርስቶስ ይመሰክሩላቸው ጀመር፡፡ ጥቂቶቹም ሚሲዮናውያንና ወንጌላውያን ሆኑ፡፡ በዚህ መንገድ፣ ሐዋርያት ራሳቸውን የማብዛታቸውን ሥራ በየትውልዱ እውነተኛ ወንጌልን የማድረስ ስልት አደረጉት፣ አብዛኛውንም ሥራ ታከናውን የነበረው ቤተክርስቲያን ራሷ ነበረች፡፡ ቤተክርስቲያን ግን የሐዋርያትን አገልግሎት ያጅበው በነበረው ዓይነት ሥልጣንና ተዓምራዊ ማረጋገጫ የወንጌልን አገልግሎት መፈፀም እንዳልቻለች እርግጥ ነው፡፡ ሆኖም፣ መንፈስ ቅዱስ ዛሬም ቢሆን በቤተክርስቲያን እውነተኛ የሕይወትና የቃል ምስክርነት አማካይነት ሊሠራ፣ በዚህም አዳዲስ አማኞችን ሊያመጣ ፈቃደኛ ነው፡፡

ለምሳሌ፣ በስደት ስለተበታተኑት አማኞች የሐሥ 11፡19-21 የሚናገረውን አድምጡ፡

> ***በእስጢፋኖስም ላይ በተደረገው መከራ የተበተኑት እስከ ፊንቄ እስከ ቆጵሮስም እስከ አንጾኪያም ድረስ ዞሩ፥ ቃሉንም ለአይሁድ ብቻ እንጂ ለአንድ ስንኳ አይናገሩም ነበር።***
> ***ከእነርሱ ግን የቆጵሮስና የቀሬና ሰዎች የነበሩት አንዳንዶቹ ወደ አንጾኪያ መጥተው የጌታን የኢየሱስን ወንጌል እየሰበኩ ለግሪክ ሰዎች ተናገሩ።***
> ***የጌታም እጅ ከእነርሱ ጋር ነበረ፤ ቍጥራቸውም እጅግ የሚሆን ሰዎች አምነው ወደ ጌታ ዘወር አሉ። (የሐሥ 11፡19-21)***

ይህንን የሐዋርያትን አካላዊ ውሱንነት በልቡናችን በመያዝ፣ በመዋቲነታቸው ምክንያት ያለባቸውን የዝመን ውሱንነት እንመለከታለን፡፡

**የዘመን ውሱንነት**

ሐዋርያት መቼ እንደሆነ አይወቁ እንጂ ኢየሱስ ተመልሶ እንደሚመጣ ያውቃሉ፡፡ በሐሥ 12 ንጉሥ ሄሮድስ ሐዋርያውን ያዕቆብን ካስገደለው በኋላ፣ ቢያንስ አንዳንድ ሐዋርያት ኢየሱስ እስኪመለስ በሕይወት እንደማይኖሩ ገሃድ ሆነ፡፡ ስለዚህ፣ ቤተክርስቲያን በሐዋርያት የቅርብ ክትትል ብቻ ሳይሆን እነርሱ ካለፉም በኋላ ወንጌልን የማድረሱንና ቤተክርስቲያንን የመገንባቱን ሥራ እንድትሠራ ቤተክርስቲያንን አሰለጠኑ፡፡

ለምሳሌ፣ በሐሥ 20፡25-28፣ ጳውሎስ ለኤፌሶን መሪዎች የተናገረውን አድምጡ፡

> ***አሁንም፥ እነሆ፥ እኔ የእግዚአብሔርን መንግሥት እየሰበክሁ በመካከላችሁ የዞርሁ ሁላችሁ ከእንግዲህ ወዲህ ፊቴን እንዳትዩ አውቃለሁ።***
> ***ስለዚህ እኔ ከሰው ሁሉ ደም ንጹሕ እንደ ሆንሁ ዛሬ በዚች ቀን እመሰክርላችኋለሁ።***
> ***የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ ነግሬአችኋለሁና፥ ምንም አላስቀረሁባችሁም።***
> ***በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ።***
> ***(የሐሥ 20፡25-28)***

ቤተክርስቲያን እውነተኛ የወንጌል ምስክር የመሆኗን እና ያመኑትን ወደ ብስለት የማድረሷን ኃላፊነት ለመወጣት በክርስቶስ መታመኗን እንድትቀጥል ጳውሎስ ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ፣ እርሱ ከሞተም በኋላ መሪዎቿ አገልግሎታቸውን ለመቀጠል ዝግጁ መሆን እንዳለባቸው ያረጋግጥላቸዋል፡፡ ሐዋርያት በዘመን የተገደቡ በመሆናቸው ምክንያት፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋፋት ሐዋርያት የሚነድፏቸውን የአጭር ጊዜና የረጅም ጊዜ ስልቶች ለማስፈፀም ማዕከሏ ቤተክርስቲያን ነበረች፡፡

እውነተኛ ምስክር ከመሆን አንፃር ስለ ቤተክርስቲያን አስፈላጊነት ከተነጋገርን፣ ቤተክርስቲያን በሐዋርያት አማካይነት ስላደረገችው ዝግጅት ወደ መነጋገሩ እንሸጋገር፡፡

# ዝግጅት

የእግዚአብሔርን መንግሥት የማስፋፋቱን ሥራ ቤተክርስቲያን እንድትቀጥል ሐዋርያት በብዙ መንገዶች አዘጋጅተዋታል፡፡ ከጊዜ ውሱንነት የተነሳ ግን ሦስቱን ብቻ እንመለከታለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ቤተክርስቲያን ለሐዋርያት አስተምህሮ ተዓማኒ ሆና እንድትቀጥል ሐዋርያት የሰጧትን ትዕዛዝ እናያለን፣ ይህም የክርስቶስ ታማኝ ምስክር መሆንን ያካትታል፡፡ ሁለተኛ፣ ሐዋርያት የቤተክርስቲያንን ቢሮዎች፣ ሽማግሌዎችና ዲያቆናትን የመሳሰሉትን ለመሰየም ያደረጉትን እንመረምራለን፡፡ ሦስተኛ፣ ያለጥርጥር ከፊት በሚጠብቃት መከራ ውስጥ እንድትፀና ሐዋርያት እንዴት እንዳዘጋጇት እናያለን፡፡ በመጀመሪያ ሐዋርያት ለቤተክርስቲያንን ያስተላለፉትን ትምህርት እንመልከት፡፡

**ትምህርት**

በኤፌሶን ምዕራፍ 2 ውስጥ፣ ጳውሎስ ቤተክርስቲያንን ክርስቶስ እንደ ማዕዘን ራስ፣ ሐዋርያትና ነቢያት ደግሞ እንደመሠረት ሆነውላት እንደተመሠረተች ህንፃ ይመስላታል፣ በኤፌ 2፡19-20 የተናገረውን አድምጡ፡

***እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም። በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፥ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ (ኤፌ 2፡19-20)***

ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ሐዋርያት የቤተክርስቲያን የመጀመሪያ መሪዎች የነበሩ መሆናቸውን ብቻ ሳይሆን፣ ትምህርታቸው የቤተክርስቲያን መሠረት፣ የቤተክርስቲያን የእምነት መሠረት መሆኑንም ጭምር ነው።

በኤፌ 3፡4-6፣ የእርሱ ትምህርት የነበረውን የመሠረትነት ተግባር ጳውሎስ እንዲህ ይገልጠዋል፡

***ይህንም ስታነቡ የክርስቶስን ምሥጢር እንዴት እንደማስተውል ልትመለከቱ ትችላላችሁ፤ ይህም፥ አሕዛብ አብረው እንዲወርሱ፥ በአንድ አካልም አብረው እንዲሆኑ፥ በወንጌልም መስበክ በክርስቶስ ኢየሱስ በሆነ የተሰፋ ቃል አብረው እንዲካፈሉ፥ ለቅዱሳን ሐዋርያትና ለነቢያት በመንፈስ አሁን እንደ ተገለጠ በሌሎቹ ትውልዶች ዘንድ ለሰው ልጆች አልታወቀም። (ኤፌ 3፡4-6)***

ቤተክርስቲያን ራሷን ለሐዋርያት ትምህርት ማስገዛት እንደሚገባት ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ አፅንዖት በመስጠት ያሰመረበት በዚህ ምክንያት ነው። በሐሥ 2፡42 እንዲህ ዘግቦታል፡

***በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር። (ሐሥ 2፡42)***

የክርስቶስ እውነተኛ ምስክር ለመሆን፣ መንግሥቱን የማስፋፋት ጥረታችንን እግዚአብሔር እንዲባርክ፣ ቤተክርስቲያን በክርስቶስ የማዕዘን ድንጋይነት ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በቀደሙቹው ቤተክርስቲያን ሐዋርያትና ነቢያት ትምህርቶችም ላይ ልትመሠረት የሚገባት መሆኑን አንባቢዎቹ እንዲረዱለት ሉቃስ ይፈልጋል። ሐዋርያት የኢየሱስን ትምህርቶችና ሥራዎች በሥልጣንና በተዓማኒነት አስተላልፈውልናል። ስለዚህ፣ በየትኛውም ዘመን የሚኖሩ ክርስቲያኖች፣ የሐዋርያትን ትምህርቶች ሊያውቁ፣ ሊጠብቁና ሊኖሩባቸው ይገባል።

ይህ ነገር ለዛሬዋም የክርስቶስ ቤተክርስቲያን እውነትነት አለው። ይህ ነገር ለእኛ ዛሬ እውነት እንደሆነ የምናረጋግጥበት ግልፅ የሆነው መንገድ አዲስ ኪዳን ራሱ በተቀዳሚነት የተፃፈው በሐዋርያት መሆኑ ነው። ደግሞም በሐዋርያት ያልተፃፉት ማለትም እንደ ሐዋርያት ሥራ የመሳሰሉት የሐዋርያት ይሁንታ ያለባቸው ናቸው። በዚህ ዘመን እንደምትገኝ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን፣ ሕይወታችን የሐዋርያት ትምህርት እውነተኛ ማጠቃለያ በሆነው በአዲስ ኪዳን ጽሑፍ ላይ ሊገነባ ይገባል።

ለእነርሱ ትምህርት ታማኝ ሆና እንድትዘልቅ በማዘዝ ሐዋርያት ቤተክርስቲያንን እንዳዘጋጁት ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ቤተክርስቲያን ወደ አዳዲስ ድንበሮች እና ትውልዶች ትዘልቅ ዘንድ አገልጋዮችን እንዴት ማሳደግ እንዳለባት በማሳየት ቤተክርስቲያንን ያዘጋጁበትን መንገድ እንመለከታለን።

## ቢሮዎች

እንደተመለከትነው፣ ሐዋርያት የተሰጣቸውን ተልዕኮ በራሳቸው ብቻ ለመፈፀም እንዳችሉ አካላዊ እና የዘመን ውሱንነት ነበረባቸው፡፡ ለዚህ ችግር መፍትሄ የሚሆነው አንዱ ነገር በቤተክርስቲን ውስጥ ተጨማሪ አገልጋዮችን ማሳደግ ነው፡፡

በዚህ ላይ ቆመ ብለን የተለያዩ ክርስቲያናዊ ትውፊቶች የቀደመችውን ቤተክርስቲያን አስተዳደርና ቢሮዎች በተለያዩ መንገዶች እንደሚረዷቸው መናገር እንወዳለን፡፡ አንዳንድ ቤተክርስቲያናት ለሦስት ቢሮዎች ብቻ እውቅና ይሰጣሉ፡ ጳጳስ፣ ሽማግሌ እና ዲያቆን፡፡ ሌሎች ደግሞ ሁለቱን ብቻ ማለትም ሽማግሌና ዲያቆንን ይቀበላሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ሐዋርያ፣ ሚሲዮናዊ፣ ወንጌላዊና ሌሎችንም ያካትታሉ፡፡

የቤተክርስቲያን አግባብነት ያለው አስተዳደር ጥያቄ ከዚህ ትምህርት አድማስ እጅግ የዘለለ ነው፣ ሆኖም ሐዋርያት ተጨማሪ ቢሮዎችን በቤተክርስቲያን የሰየሙት ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔርን ተልዕኮ በትክክል መወጣቷን ለማረጋገጥ የመሆኑን ጥቅል ነጥብ ማንሳት እንወዳለን፡፡

እንዲያውም፣ ሐዋርያት ተጨማሪ ቢሮዎችን መሰየም የጀመሩት ወዲውኑ ነበር ምክንያቱም በኢየሩሳሌም በምትገኘው ቤተክርስቲያን ውስጥ ሊከናወኑ የሚገባቸውን የቤተክርስቲያን ሃላፊነቶች ብቻቸውን መወጣት እንደማይችሉ በፍጥነት ተረድተው ስለነበር ነው፡፡ ይህንንም በሐሥ 6፣ ቤተክርስቲያን የአባላቷን ፍላጎት በትክክል ታሟላ ዘንድ ሐዋርያት የዲቆናትን ቢሮ ሲሰይሙ በግልፅ እንመለከተዋለን፡፡ በዚህ ረገድ፣ በየዕለቱ የሚከናወነውን የምግብ ማከፋፈል ሥራ የሚወጡ ወንዶችን ቤተክርስቲያን እንድትመርጥ ሐዋርያት ትዕዛዝ ሰጥተዋል፡፡

በሐሥ 6፡3-6 ሐዋርያት ለዚህ ጉዳይ መፍትሄ የሰጡበትን መንገድ አድምጡ፡

> ***ወንድሞች ሆይ፥ በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ፥ ለዚህም ጉዳይ እንሾማቸዋለን፤ እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን።***
> ***ይህም ቃል ሕዝብን ሁሉ ደስ አሰኛቸው፤ እምነትና መንፈስ ቅዱስም የሞላበትን ሰው እስጢፋኖስን ፊልጶስንም ጵሮኮሮስንም ኒቃሮናንም ጢሞናንም ጳርሜናንም ወደ ይሁዲነት ገብቶ የነበረውን የአንጾኪያውን ኒቆላዎስንም መረጡ።***
> ***በሐዋርያትም ፊት አቆሙአቸው፥ ከጸለዩም በኋላ እጃቸውን ጫኑባቸው። (የሐሥ 6፡3-6)***

ሐዋርያት በተጨማሪም ፓስተሮች ብለን የምንጠራቸውንና የቤተክርስቲንን የተለያዩ ማኅበረ-ምዕመናን እንዲያስማሩና እንዲመሩ ሽማግሌዎችን ሾመዋል፡፡ ለምሳሌ፣ በጳውሎስ ሚሲዮናዊ ጉዞዎች ወቅት፣ ሐዋርያው አዳዲስ አማኞችን ያሰባስብና ቤተክርስቲያን በመመሥረት፣ እርሱ ከስፍራው ሲሄድ የቤተክርስቲያንን ኃላፊነት የሚወጡ መሪዎችን ይሰይማል፡፡

የዚህን ምሳሌ በሐሥ 14፡23 ውስጥ እንመለከታለን፣

> ***በየቤተ ክርስቲያኑም ሽማግሌዎችን ከሾሙላቸው በኋላ ጠመውም ከጸለዩ በኋላ፥ ላመኑበት ለጌታ አደራ ሰጡአቸው። (የሐሥ 14፡23)***

እንዲያውም፣ ሐዋርያት እነርሱ ባሉበትም ስፍራ እንኳን ለቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችን በማዘጋጀቱ ረገድ ቁርጠኞች ነበሩ ምክንያቱም በአጠገባቸው ሆነው ለማበረታታት ነበር፡፡ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የምናገኘው የዚህ ነገር ዐቢይ ምሳሌ፣ ሐዋርያት በቤተክርስቲያን ውስጥ እንዴት ይሳተፉ ለሚለው የአህዛብ ጥያቄ መልስ ለመስጠት በተጠራው የኢያሩሳሌም ጉባኤ ተገልጧል፡፡ ጉባኤው በሐዋርያትና በሽማግሌዎች የተመራ ነበር፡፡ ይህ ወቅት በተዘገበበት በሐሥ 15 ውስጥ፣ ሐዋርያትና ሽማግሌዎች በአንድነት እንደ ቤተክርስቲያን መሪ አምስት ጊዜ ተጠቅሰዋል፡፡

በሐሥ 15፡1-2 ምዕራፉ እንዴት እንደሚጀምር አድምጡ፡

> ***አንዳንዶችም ከይሁዳ ወረዱና። እንደ ሙሴ ሥርዓት ካልተገረዛችሁ ትድኑ ዘንድ አትችሉም ብለው ወንድሞችን ያስተምሩ ነበር።***
> ***በእነርሱና በጳውሎስ በበርናባስም መካከል ብዙ ጥልና ክርክር በሆነ ጊዜ፥ ስለዚህ ክርክር ጳውሎና በርናባስ ከእነርሱም አንዳንዶች ሌሎች ሰዎች ወደ ሐዋርያት ወደ ሽማግሌዎችም ወደ ኢየሩሳሌም ይወጡ ዘንድ ተቈረጠ። (የሐሥ 15፡1-2)***

ጳውሎስና ሌሎች ከሐዋርያትና ከሽማግሌዎች ጋር እንዲመካከሩ ተልከው ነበር፡፡ በተመሳሳዩ ምዕራፍ በቁጥር 4፣6፣22 እና 23 ውስጥ ተመሳሳይ ሐረጎችን እናገኛለን፡፡

በሐዋርያት ሥራ በጠቅላላ፣ መሲሃዊውን የእግዚአብሔር መንግሥት ተልዕኮ እንዲፈፅሙ በቤተክርስቲያን ቢሮዎች ለተሰማሩ አገልጋዮች ሐዋርያት ጥሪ ሲያቀርቡላቸው ትመለከታላችሁ፡፡ ይህንንም ጳውሎስ ለኤፌሶን መሪዎች አደራውን ባስተላለፈበት በሐሥ 20 ውስጥ እናገኘዋለን፡፡ ደግሞም በሐሥ 15 እና 21 የቤተክርስቲያን አዕማድ በሆኑት ያዕቆብን በመሳሰሉ ሽማግሌዎች ድርሻም ውስጥ ተጠቅሶ እናየዋለን፡፡

ጳውሎስ በቲቶ 1፡5 ስለ እነዚህ አገልጋዮች አሿሿም የተናገረውን አድምጡ፡

> ***ስለዚህ ምክንያት የቀረውን እንድታደራጅ በየከተማውም፥ እኔ አንተን እንዳዘዝሁ፥ ሽማግሌዎችን እንድትሾም በቀርጤስ ተውሁህ፤ (ቲቶ 1፡5)***

ጳውሎስ ራሱ ሳይጨርስ የቀረውን ነገር ያደራጅ ዘንድ ወጣቱን መጋቢ ቲቶን ጳውሎስ መመሪያ ይሰጠዋል፡፡ ማለትም፣ ጳውሎስ የጀመረውን ሽማግሌው ቲቶ ሲጨርሰው፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል የማስፋፋቱን ሐዋርያዊ ተልዕኮ ይቀጥላል ማለት ነው፡፡

ጳውሎስና ሌሎች ሐዋርያት እነዚህን ቢሮዎች ሲሰይሙ አገልጋዮቹ አገልግሎቱን ከእነርሱ እንዲረከቡ ነበር፡፡ ሐዋርያት ሁሉን ነገር እነርሱ ብቻ እንዲፈፅሙ የእግዚአብሔር እቅድ አልነበረም፡፡ ለሐዋርያት ያቀደላቸው ቤተክርስቲያንን እንዲመሠርቱ ነበር፡፡ ከእነርሱ የቤተክርስቲያንን አመራር ሊረከቡ የሚችሉ ሌሎችን እንዲያሰለጥኑ፣ ሐዋርያት በመሠረቱት ላይ መገንባት የሚችሉ አገልጋዮችን እንዲያፈሩ፣ ሐዋርያት ሊደርሱባቸው በማይችሉ ጊዜዎችና ስፍራዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚያስፋፉትንም እንዲያሰለጥኑ አቅዶላቸው ነበር፡፡

እስካሁን ድረስ ሐዋርያት የኢየሱስን ሥራዎችና ትምህርቶች ለቤተክርስቲያን ማስተማራቸውን እና የክርስቶስን ተልዕኮ የሚያሳኩ ተጨማሪ አገልጋዮችን ማሳደጋቸውን ተመልከተናል፡፡ በዚህ ወቅት ደግሞ፣ ቤተክርስቲያን ወደፊት እየገፋች ስትሄድ የሚጠብቃትን የማይቀረውን መከራ እንዴት ልትጋፈጠው እንደሚገባ ሐዋርያት ቤተክርስቲያንን ያዘጋጁበትን መንገድ እንነጋገርበታለን፡፡

## መከራዎች

ሉቃስ የሐዋርያትን ተግባር የሚገልጠው ንቀት የጠገቡበት፣ አደጋና ስደትን የተጋፈጡበት ነበር ብሎ ነው፡፡ ደግመው ደጋግመው ታስረዋል ተደብድበዋልም፡፡ ሐዋርያው ያዕቆብም በንጉሥ ሄሮድስ ተሰይፏል፡፡ በእነርሱ ሕይወት እውን የነበረው ሁሉ በተቀሩት ክርስቲያኖችም ሕይወት እውን እነደሚሆን ሐዋርያት ያውቁ ነበር፡፡

በአንድ ይህንን በግልፅ በሚሳይ ትዕይንት፣ ማለትም ጳውሎስ በልስጥራ በቁጣ በነደዱ በማያምኑ ሰዎች በድንጋይ ተወግሮ በሞት አፋፍ ተጥሎ እናያለን፡፡ በሚቀጥለው ቀን፣ ወደ አጎራባቿ ከተማ ወደ ደርቤ ሸሽቷል፡፡ ብዙም ሳይቆይ ግን፣ ወደ ልስጥራ እና ሌሎች ከተሞች በመመለስ አማኞችን ያበረታታ ነበር፡፡

ሉቃስ የሐሥ 14፡21-22 ያለውን የዘገበው በጳውሎስ ሕይወት ላይ በተደረገው ሙከራ አውድ ውስጥ ነበር፡

> ***በዚያችም ከተማ ወንጌልን ሰብከው እጅግ ደቀ መዛሙርትን ካደረጉ በኋላ፥ የደቀ መዛሙርትን ልብ እያጸኑ በሃይማኖትም ጸንተው እንዲኖሩ እየመከሩና። ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል እያሉ፥ ወደ ልስጥራን ወደ ኢቆንዮንም ወደ አንጾኪያም ተመለሱ። (ሐሥ 14፡21-22)***

ሐዋርያት የሚፈልጉት ቤተክርስቲያን መከራና ስደት የሚጠብቃት መሆኑን እንድትረዳ ነው፡፡ ጥቂቶቹም ስለ እምነታቸው ሊሞቱ እንኳን ይችላሉ፡፡ የመንግሥቱ ግብም ይህንን ያጠይቃል፣ ይገባዋልም፡፡ ስለዚህም፣ ቤተክርስቲያን ለክርስቶስ በፅናት ታማኝ ሆና ልትዘልቅ ይገባታል፡፡

ቤተክርስቲያን መከራን እንድትጋፈጥ ሐዋርያት ያዘጋጁበት መንገድ ጳውሎስ ለኤፌሶን መሪዎች ባደረገው የታወቀ ንግግርም ውስጥ ይታያል፡፡ በሐሥ 20 ውስጥ፣ ጳውሎስ ምናልባት ደግመው ሊያዩት እንደማይችሉ ይነግራቸዋል፡፡ ወደ ኢሩሳሌም እንደሚሄድ፣ በዚያም እንደሚታሰር አልፎም ሊገደልም እንደሚችል ይነግራቸዋል፡፡ ጳውሎስ በዚህ አሰቃቂ የራስ ሕይወት አመለካከት አውድ ውስጥ፣ የኤፌሶንን ቤተክርስቲያን ስለሚጠብቃት መከራ ማስጠንቀቂያም ማሳሰቢያም ይሰጣል፡፡

በሐሥ 20፡28-31፣ ለኤፌሶን መሪዎች እንዲህ ይላል፡

> ***በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቋአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ፥ ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሡ እኔ አውቃለሁ።***
> ***ስለዚህ ሦስት ዓመት ሌሊትና ቀን በእንባ እያንዳንዳችሁን ከመገሠጽ እንዳላቋረጥሁ እያሰባችሁ ትጉ። (ሐሥ 20፡28-31)***

የተለያዩ ሐዋርያት ለቤተክርስቲያን በጻፏቸው የተለያዩ ደብዳቤዎች ውስጥ ተመሳሳይ ነገሮችን ጠቅሰዋል፡፡ ጴጥሮስ፣ ዮሐንስ እና ጳውሎስ አብያተክርስቲያናት የእምነት ጠላቶችን በንቃት እንዲጠብቁ፣ በቅዱሳት መጻሕፍትና በትምህርቶቻቸው እንዲደገፉ እና ለክርስቶስ ታማኝ ሆነው እንዲዘልቁ አሳስበዋል፡፡

በነዚህ ሁሉ ውስጥ፣ የሐዋርያት ዓላማ ቤተክርስቲያንን ተስፋ ማስቆረጥ አልነበረም፡፡ ይልቁኑ፣ በመከራ ውስጥ ክርስቶስን በመታመን እንዲዘልቁ፣ በመንፈስ ቅዱስ የፀጋ ስጦታዎች እንዲታመኑ እና የእግዚአብሔርን ተልዕኮ እንዲቀጥሉና እንዲገፉበት አብያጠክርስቲያናትን ለማዘጋጀት ነው፡፡

ቤተክርስቲያንን በሐዋርያት ምስክርነትና አስተምህሮ በመመስረት፣ አገልጋዮችንም በቤተክርስተያን ውስጥ በማሰማራት፣ ቤተክርስቲያንን በመከራ ውስጥ እንድትፀና በማዘጋጀት እና በሌሎችም መንገዶች፣ በየትኛውም ዘመንና ስፍራ የምትገኝ ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔርን መንግሥት የማስፋፋቱን ተልዕኮ ልትፈፅም እንደምትችል ሐዋርያት ዋስትና ይሰጧታል፡፡

# 5. ማጠቃለያ

በዚህ ትምህርት በሐዋርያት ሥራ ውስጥ እርስ በርሳቸው የተሸመኑ ሦስት ዐበይት መሪ ሃሳቦችን ዳስሰናል፡፡ የመንፈስ ቅዱስን እንቅስቃሴና ስጦታ ተመልክተናል፡፡ ሐዋርያትን እንደ ልዩ የክርስቶስ ባለሙሉ ሥልጣን ምስክሮች የመመልከቱን አስፈላጊነት ተመልክተናል፡፡ ደግሞም ቤተክርስቲያንን በመመሥረት ሐዋርያት የተሰጣቸውን ተግባር እንዴት እንደፈፀሙ ተመልክተናል፡፡

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የታሪክና የነገረ-መለኮት አስደናቂ ሥራ ነው፡፡ ሉቃስ ለቴዎፍሎስና ለቀደመችው ቤተክርስቲያን ሲፅፍ፣ የመንግሥቱን ወንጌል በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በምድር ለሚገኙ ህዝቦች ሁሉ በመመስከር የማስፋፋቱን አስፈላጊነት አስምሮበታል፡፡ እነዚህኑ ተመሳሳይ ትምህርቶች ዛሬ በእኛ ሕይወት ስናዛምዳቸው፣ እኛም ራሳችንን ለእግዚአብሔር መንግሥት እንድናስገዛ፣ ዘላለማዊ መንግሥቱንም ለመመሥረት ክርስቶስ ዳግመኛ የሚመለስባትን ቀን ልንጠባበቅ ይገባናል፡፡